

# የ ይህ ነው
# የኛ
# ኢስላም

## ማብራሪያ

ደራሲ
ዐቀበተ ኢስላም ኑረዲን

## ማውጫ ገፅ


መግቢያ ... 2

የማያልቀው ክስ ... 3

ከኢ-አማኞች ጋር ያለ ሽሪዓዊ መስተጋብር ... 5

የጦር አንቀፃት እውነታ ... 8

በጣትህ ስትጠቁም፤ ሶስቱ ወደ አንተ ነው! ... 14

የጂሐድ ህግጋት ... 19

ጂሐድ በ"ፍትሐዊያን" ዓይን ... 24

ኊልቆ ሰማዕታት ... 26

የእስራኤላዊያን ጉዞና የፍስጤማዊያን መጨፍጨፍ ... 30

የእስራኤላዊያን ወረራ ባህሪያት ... 35

ማጠቃለያ ... 38

# መግቢያ

በሀይማኖት ንፅፅር ጥናት ውስጥ በክርስቲያን አጥኚዎች (Christian Apologists) ከሚቀርቡ ክሶች ተደጋጋሚና አሰልቺ ከሆኑት አንዱ የጂሐድ ፅንሠ ሀሳብና ተያያዥ ነጥቦች ናቸው። ሙስሊም አጥኚዎችና ሙህራን በተለያየ መልኩ ተገቢውን መልስ የሰጡ ቢሆንም ከሳሾችም የተለያዩ "ቅመሞችን" በመጨመር እንደ አድስ ሲያነሱትና ሲጥሉት በሌሎች አስፈላጊ ርዕሶች ላይ የሚደረጉ ጥናቶችን ከርዕስ ለማስወጣትና ለክርክር ማሟሟቂያ ሲያደርጉት ይስተዋላል። ይህ ፅሁፍ"ትንቢተ-ነቢዩ ሙሀመድ፡ ንፅፅራዊ አቀራረብ"[1] ከሚለው ዳጎስ ያለ መፅሀፌ የተወሰደ ሲሆን በዋና መፅሀፉ በነቢዩ ሙሀመድ ነቢይነት ላይ በሚቀርቡ ክሶች ላይ መልስ ከሰጠሁባቸው "ውዝንብሮች" አንዱ ነው። የዚህ ፅሁፍ ዋና መነሻ የታላቁ ኢትዮጵያዊ ምሁር የሸይኽ ኢልያስ አህመድ "ይህ ነው የኛ ኢስላም" ጥናት ነው። በፅሁፉ ውስጥ የሸይኹን ጥናት እንዳለ የወሰድኩ ሲሆን ሌሎች ደጋፊ ማስረጃዎችንና ማብራሪያዎችን ደግሞ በግርጌ ማስታዎሻ አስፍሬያለው። በሸይኹ ፅሁፍም ላይ ይሁን በሌሎች ፀሀፊዎች የተጨመረ ርዕስ የእኔ መሆኑንም ከወድሁ ማረጋገጥ እፈልጋለሁ።

[1] ትንቢተ ነቢዩ ሙሀመድ፡ ንፅፅራዊ አቀራረብ፡ ገፅ 231 — 240

# የማያልቀው ክስ

ለፅሁፌ መነሻ የሆነኝ ከሳሽ መምህር ኪዳነ ማሪያም 'መፅሀፍ ቅዱስና ሙሀመድ አይተዋወቁም' በሚለው መፅሀፋቸው "*ሙሀመድ ሃይማኖቱንና ነቢይነቱን የጫነባቸው ታሪኩ እንደሚያስረዳው ወገኖቹን ዐረቦችን እንደበርሃ ግመል በጦር ኃይል አንበርክኮ ነው እንጂ አስወድዶና አስፈቅዶ እንዳልነበር ይታወቃል።*" [2] በማለት በብዙ መልኩ መልስ የተሰጠበትን 'የድሮ ክስ' እንደ አዲስ ከፍተዋል። አጥኚዎች እስልምና በሰይፍ እንደተስፋፋ መለፈፍና ሙስሊሞችን በአክራሪነትና በገዳይነት መክሰስ መነሻው የመስቀል ጦርነት መሆኑንና ያስጀመሩትም የቤዛንታይን ጳጳሳት መሆናቸውን ይገልፃሉ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ክሱ ያለምንም ለውጥ አቅጣጫውን እየቀያየረ"የሙስሊሞች መገለጫ"ሆኖ ተስሎ ቆይቷል። በየትኛውም የአሜሪካና በሌሎችም ፊልሞች በጃኬታቸው ስር ቦንብ በታጠቁ ህፃናት የተሞላው የዚሁ ፕሮፓጋንዳ ውጤት ነው። ሸይኽ ኢልያስ አህመድ ለዚህና መሰል ክሶች መልስ ሲሰጥ እንዲህ ብሏል።

"*ስለ አንድ ሀይማኖት እውነተኛ ይዘት ለመረዳት ወደ ትክክለኛ መዛግብቱና ምንጮቹ መመለስ አማራጭ የሌለው እርምጃ ነው። ይህ ሲሆን ግን መመሪያዎቹንና አንቀፆቹን በቁንፅል እይታና በጥራዝ ነጠቅ መዘዛ እየገመገሙ ለፍርድ መቻኮል ታላቅ ስህተትን ያወርሳል፤ ለበደልም ያበቃል። የእምነቱን ሁለንተናዊ ይዘትና አስተምህሮት መገንዘብ የሚቻለው አናቅፁን በታትኖ ሳይሆን ሰብስቦ፣ አራርቆም ሳይሆን አቀራርቦ ነውና። በአንድ ቦታ ያልተብራራው በሌላ ቦታ ይብራራል፤ እዚህ ጋር ያልተገደበውም እዚያ ጋር ሊገደብ ወይም መስፈርቱ ሊገለፅ ይችላል። ከዚህም ጋር ቃሉ የተነገረበትን አገባብና አኳያ ማስተዋል የግድ ነው።*

[2] መፅሀፍ ቅዱስና ሙሀመድ አይተዋወቁም፡ ገፅ 9

*በጥናት ሂደት ላይም በአሻሚ ገለፃዎች ላይ ከመንጠልጠል ወደ ግልፅ መመሪያዎች መመለስ ይገባል። ይህን መተግበር የአንድ ዘርፍ ምሁራን ከሰርጎ ገቦች ከሚለዩባቸው ነጥቦች አንዱ ነው።*

## ከኢ-አማኞች ጋር ያለ ሸሪዓዊ መስተጋብር

*ይህን እንደመግቢያ ከተረዳን ዘንድ ወደ አንድ ሁነኛ ምሳሌ እንሸጋገር፦*

*ሙስሊሞች ከሌሎች እምነት ተከታዮች ጋር በሚኗኗሩበት ሂደት ሊከተሉት ስለሚገባቸው አጠቃላይ ስርዓት ኢስላም ያሰፈረውን ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለው በጦረኛ ጠላቶች ላይ ውጊያ በታወጀባቸው አንቀፆች በኩል አይደለም።*[3] *እነዚህ በውስን የጦርነት ሂደት ላይ ብቻ ሊተገበሩ የሚችሉና በተለያዩ ቅድመ ሁኔታዎች የተከበቡ ህግጋት እንጂ የሁልጊዜ ደንቦች አይደሉም።*

[3] ሊቃውንት አንድ ሙስሊም ከኢ-አማኒያን ጋር እንደት መኗኗር እንዳለበት በተለያዩ ህጎችና ደንቦች እንደደነገገ ይገልፃሉ። ከበርካታ ህግጋት ውስጥ ለዚህ ፅሁፍ ይመጥናል ያልኳቸውን ጥቂቶቹ

1, እኩልነት፦- አምላካችን አላህ በተከበረ ቃሉ"አላህ በማስተካከል፣ በማሳመርም፣ ለዝምድና ባለቤት በመስጠትም ያዛል። ከአስከፊም (ከማመንዘር)፣ ከሚጠላም ነገር ሁሉ፣ ከመበደልም ይከለክላል። ትገነዘቡ ዘንድ ይገስጻችኋል።"(አን ነህል 16:90) በሌላ አንቀፅም"ሕዝቦችንም መጥላት ባለማስተካከል ላይ አይገፋፋችሁ። አስተካክሉ። እርሱ (ማስተካከል) ለአላህ ፍራቻ በጣም የቀረበ ነው።"(ማኢዳህ 5:8) በማለት ለየትኛው የሰው ልጅ ፍትሐዊ እንድንሆን አዟል። በዚህም መሰረት ሙስሊሞች የሌላ እምነት ተከታዮችን በምንም መልኩ ተፅዕኖ እንዳያደርጉ፣ ኢ-አማኞች በህግ ፊት እኩል እንዲዳኙ፣ የንብረት፣ በህይወት የመኖር መብታቸው በአግባቡ እንዲከበር አዟል።

2, በሀይማኖት ማስገደድ የለም፦- አምላካች በተከበረ ቃሉ"በሃይማኖት ማስገደድ የለም። ቅኑ መንገድ ከጠማማው በእርግጥ ተገለጠ።"(አል በቀራህ 2:256) በማለት አስገድዶ ማስለም እንደማይቻል ነግሮናል። በእስልምና አንድ ሰው ማንኛውም መልካም ስራው በአላህ ዘንድ ተቀባይነት ይኖረው ዘንድ ሁለት መስፈርቶችን ማሟላት አለበት። ኒያ (ስራን ለአላህ ብሎ መስራት) እና ሙታበዓህ (የነቢዩን ፈለግ መከተል)። ሆኖም ተገዶ የሰለመ ሰው እነዚህን ሁለት መስፈርቶች ማሟላት በፍፁም አይችልም። በመሆኑም ሰዎችን አስገድዶ ማስለም አይቻልም።

3, በሰላምና በፍቅር መኗኗር፦- ኢስላማዊ ትዊፊቶች በሙሉ ሙስሊሞች ቃል ኪዳን ከገቡና የሰላም ስምምነት ከፈፀሙ ከሰላማዊ ኢ-አማኒያን ጋር በሰላምና በፍቅር እንዲኗኗሩ ያዛሉ። አምላካችንም"ከእነዚያ በሃይማኖት ካልተጋደሏችሁ ከአገሮቻችሁም ካላወጡዋችሁ (ከሓዲዎች) መልካም ብትውሉላቸውና ወደእነርሱ ብታስተካክሉ አላህ አይከለክላችሁም።

*ይህንን ከሚያብራሩት አንቀፆች መካከል የሚከተለው ይገኝበታል፦"ለእነዚያ በሀይማኖታችሁ ላልተጋደሏችሁና ከአገራችሁ ላላስወጧችሁ በጎ ብታደርጉና ፍትህን ብትውሉ አላህ አይከለክላችሁም፤ አላህ ፍትኸኞችን ይወዳልና። አላህ የሚከለክላችሁ እነዚያ በሀይማኖታችሁ (የተነሳ) የተጋደሏችሁንና ከአገራችሁ ያስወጧችሁን እናንተን በማስወጣትም ላይ ያገዙትን እንዳትወዳጇቸው ነው።"*[4]

*ይህ ሌሎችን ሙስሊም ስላልሆኑ ብቻ መግደል እንደማይቻል ያሳያል፤ በየትኛውም የታሪክ ማህደር ሙስሊሞች ሌሎችን ኢስላምን ስላልተቀበሉ ብቻ ገድለው አያውቁም። በኢስላማዊ አስተዳደር ውስጥ ለምዕተ አመታት የኖሩት ሙስሊም ያልሆኑ ወገኖችም ተገድደው ኢስላምን እንዳልተቀበሉ ተጨባጩ አለም*

አላህ ትክክለኞችን ይወዳልና።"(አል-ሙምተሀናህ 60፡8) ብሏል። ከሰላማዊ ኢ-አማኒያን ጋር ጓደኝነት መመስረት፣ መጋዛት፣ ሲቸግራቸው ማገዝ፣ ሲያማቸው መጠየቅ፣ መረዳዳትና ማህበራዊ አገልግሎቶች በጋራ መመስረት በሸሪዓው ተደንግጓል።

4, በለዘብታ ቃል መጥራት፦- ቁርአን እንደሚነግረን በአላህ ዘንድ የተወደደው ሀይማኖት እስልምና ብቻ በመሆኑ ሰዎች ሁሉ ይድኑ ዘንድ እስልምናን ሊቀበሉ ይገባል። በመሆኑ ኢስላማዊ ጥሪ ሊደረግላቸው ይገባል። አምላካችን የጥሪውን ባህሪ ሲነግረን"ወደ ጌታህ መንገድ በብልሃትና በመልካም ግሳጼ (በለዘብታ ቃል) ጥራ። በዚያችም እርሷ መልካም በኾነችው (ዘዴ) ተከራከራቸው።" (አን-ነህል 16፡125) በማለት ነግሮናል።

5, የአምልኮት ነፃነት፦- ታላቁ ሶሀባ ዑመር ኢብኑል ኸጧብ ኢየሩሳሌምን በተቆጣጠሩ ጊዜ ለክርስቲያኖች የማምለኪያ ቦታ ከመስጠታቸውም ባለፈ ዋስትናም ሰጥተዋቸው ነበር። ከዚህ በመነሳት ሙስሊም ሊቃውንት ቤተ-እምነት የመገንባት፣ በአካባቢያቸው ሀይማኖታዊ በዓላትን እንዲያከብሩ የተፈቀደላቸው መሆኑን ይጠቅሳሉ።

6, ዚማ (ቃል ኪዳን)፦- ኢስላማዊ የሸሪዓ ህግ ከሌሎች የሚለየው በሁሉም ጉዳዮች ላይ የሚሰጠው ውሳኔ ነው። ከላይ ካየናቸው ጥቅል ህግጋት ባለፈ የሸሪዓ ህግ ሙስሊም ያልሆነ ሰዎች በሙስሊም አስተዳደር ውስጥ እንዴት እንደሚኖሩ አብራርቷል። በሙስሊም መንግስት ስር የሚተዳደሩ ሙስሊም ያልሆኑ ወገኖች ከሙስሊሙ መንግስት ጋር ቃል ኪዳን ይገባሉ። እነዚህ ማህበረሰቦች የቃል ኪዳን ቤተሰብ (ዚማ') ይሆናሉ። ሸይኽ ፈውዛን ስለነዚህ ማህበረሰቦች መብት ሲያብራሩ "ከስምምነቱ በኋላ ማንኛውም ሙስሊም በከሀዲዎች ላይ ድንበር ማለፍ አይችልም። ቃል ኪዳን የገቡ ከሀዲዎችን ደማቸውም (ነፍሳቸውም) ይሁን ገንዘባቸው የተከበረ ሆኖ ይቀጥላል። በሙስሊሞች ቃል ኪዳንና ጫንቃ ስር በመግባታቸው ለሙስሊሞች ያላቸው መብትም ይሁን ያለባቸው ግዴታ በእነርሱም ላይ ይኖራቸዋል።" ይላሉ። ነቢዩ ሙሀመድም በአንድ ንግግራቸው"በቃል ኪዳን የሚኖርን ኢ-አማኝ የገደለ ሰው የጀነትን ሽታ አያሸታትም፤ የጀነት ሽታዋ አርባ ዓመት (የሚያስኬድ ርቀት ላይ) ይገኛል።"(ቡኻሪ 3166) ብለዋል። ለቃል ኪዳን ነዋሪዎች የተሰጣቸው ክብር ምንያክል እንደሆነ ተመልከቱ!

[4] አል-ሙምቲሐነህ 60፡8-9

*ይመሰክራል።*[5] *ይህም ማለት የግዛቱ መተዳደሪያ ህግ ቁርኣናዊ ሆኖ ሳለ መብታቸው በጥቅሉ ተጠብቆ ነበር ማለት ነው።*

*አደራ! እንደነ isis ያሉትን ቡድኖች እዚህ ርዕስ ላይ ማስገባት ራሱ ስህተት ነው! እነርሱ ከማንም ይልቅ የገደሉት ሙስሊሞችን ነው፡!*[6] *በዚህ ላይ ደግሞ ስለማንነታቸው የምንለው፦ ውስጡን ውስጠ-አዋቂ ይወቀው፤ ነው!*[7]

---

[5] ታላቁ የንፅፅር አጥኚ ዶ.ር ዛኪር ናይክ Answer to Non-muslims'common questions about Islam በሚለው መፅሀፉ"ሙስሊሞች ስፔንን ለ800 ዓመታት ያህል አስተዳድረዋል። በስፔን የነበሩት ሙስሊሞች ሰዎችን እስልምናን እንዲቀበሉ በሰይፍ አላስገደዱም። በኋላ ግን የክርስቲያን መስቀለኞች (Crusaders) ወደ ስፔን መጥተው ሙስሊሞችን አጠፉ። በዚያ ጊዜ በስፔን ውስጥ አዛን (adhan) (ወደ ሶላት የሚደረግ ጥሪ) በግልጽ ሁኔታ ሊያሰማ የሚችል አንድም ሙስሊም አልነበረም። (በተመሳሳይ) ሙስሊሞች ህንድን ለአንድ ሺህ ዓመታት ያህል ገዝተዋል። ቢፈልጉ ኖሮ፣ በህንድ ያሉትን ሁሉንም ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎች ወደ እስልምና የመቀየር ኃይል ነበራቸው። ዛሬ ግን ከህንድ ሕዝብ 80% በላይ ሙስሊም አይደሉም። እነዚህ ሙስሊም ያልሆኑ ህንዶች ሁሉ እስልምና በሰይፍ እንዳልተስፋፋ ዛሬ ምስክር ናቸው።"ሲል ፅፏል። (ገፅ 28-29)

[6] "ሸይኽ ሷሊህ ፈውዛን- ሐፊዞሁሏህ- ደግሞ የሚከተለውን ተናግረዋል፦"ጅሐድ በእውቀት ባለቤቶች መጽሐፍት ውስጥ ስለርሷ የእውቀት ባለቤቶች እና የመረጃ ባለቤቶች የሚጠየቁባት ፣ ወደርሷ የሚመለሱባት ፣ የጅሐድ አህካም ከአላህ ኪታብና ከረሡል ﷺ ሱና የተመሰረተባት ትልቅ ክፍል አለው፡፡ ምክንያቱም የጅሐድ ጉዳይ ትልቅ ነው። አላህ በዘረጋው መሰረት ላይ ስርዓት ይዞ ከተጓዘ ፣ ጅሐድ ለኡመቱ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ያለምንም እውቀት እና የዲን ማስረጃ ስርዓት አልበኛነት ከፈጠሩበት ለኡመቱም ይሁን ለሙስሊሙ ከህመም ላይ ህመም ይሆናል፡፡ ካፊርን ለማስቆጣት በሚል ከእነርሱ በጥንካሬ የሚበልጡትን ስንት ጀሂሎች ናቸው አጥፍተው በመጥፋት በሙስሊሙ ላይ ግድያ ፣ ከአገር ለመሰደድ ፣ ለመፈራረስ ምክንያት የሆኑት? ወላሃውለ ወላ ቁወተን ኢላ ቢላህ። እነዚህ አጥፍተው የሚጠፉ ሰዎች ይህን ድርጊታቸውን ጅሐድ ብለው ይጠራሉ ፤ ይህ ጅሐድ አይደለም -ምክንያቱም መስፈርቶቹ አልተሟሉም፡፡ ማእዘናቶቹ አልተረጋገጡም ፤ ይህ ጅሐድ አይደለም- ይህ አላህ ያላዘዘው ድንበር መተላለፍ ነው።"(ከጂሐድ ጥበብና ህግጋት ምርጥ ፍሬዎች፡ ሸይኽ አብዱረዛቅ ኢብን አብዱል ሙህሲን፡ (ትርጉም፡ ዩሱፍ አህመድ)፡ ገፅ 31)

[7] አንዳንድ ክርስቲያን አፖሎጂስቶችና ሚሽነሪዎች የሽብር ቡድኖች ሙስሊም ነን ብለው ስለሞገቱ፣ መሪዎቹ ኢስላማዊ ትምህርት ስለተማሩ፣ ከቁርአንና ከሀድስ ስላጣቀሱ ብቻ ISISዎችና መሰል በኢስላም ስም የተደራጁ አሸባሪዎችን ሙስሊሞች ናቸው ብለው መፅሀፍ እስከ መፃፍ ደርሰዋል። ከዚህ አልፈውም የISIS ሙስሊሞችን ማጥቃት ቡድኑ ኢስላማዊ መሆኑን ለማስረዳት ታትረዋል። የትኛውም ኢስላማዊ አስተምህሮት ሽብርተኝነትንና የአሸባሪዎችን ተግባር የሚያወግዝ ሆኖ ሳለ የአሸባሪዎችንና የሽብር ፈላጊዎችን ማብራሪያ ኢስላማዊ በማድረግ ሽብርተኝነትን ለመደገፍ፣ ወይም ሙስሊሞችን በሙሉ ሽብርተኛ አድርጎ ለመሳል የሚደረግ የትኛውም ጥረት "ሊበሏት ያሰቧትን አሞራ ጅግራ ናት" እንደማለት ነው። አንድ ቡድን ራሱን የክርስቲያን ነፃ አውጭ አድርጎ በመሳልና ሌሎች ክርስቶያን ጀሌዎችን አስከትሎ በክርስቲያን ስም ያገኘውን ሁሉ ቢገድል ቡድኑ ክርስቲያናዊ ነው አይደለም የሚለው የሚመዘነው ተግባሩ ከመፅሀፍ ቅዱስ መሰረታዊ አስተምህሮት ጋር ይገጥማል ወይስ አይገጥምም የሚለው ተመዝኖ እንጂ የቡድኑ አመራሮች ክርስቲያንን ነን

*ይህ እውነታው ሆኖ ሳለ ጥቂት ግለሰቦች በኢስላም ስም ለሚፈፀም የደም መፍሰስ ሁሉ ክቡሩን ቁርኣን ተጠያቂ ያደርጋሉ፤ ወይም ሀማኖቱን ራሱ ይኮንናሉ። ይህንን የሚያናፍሱት አብዛኞዎቹ ሙግተኞች መረጃዎችን ከላይ በጠቆምነው መልኩ ለማገናዘብ ብቃቱ ብቻ ሳይሆን ፍላጎቱም የላቸውም!*

## የጦር አንቀፃት እውነታ

*በዚህ ረገድ በተለያዩ አጋጣሚዎች ከሚመዟቸው አንቀፆች መካከል ዋነኛው በሱረቱ-ት-ተውባህ (9ኛው ምዕራፍ) ቁጥር 5 ላይ የሚገኘው አንቀፅ ነው፤ እንደሚከተለው ይነበባል፡-"የተከበሩት ወራት ባበቁ ጊዜ አጋሪዎቹን ባገኛችኋቸው ቦታ ግደሏቸው፤ ያዟቸውም፤ ክበቧቸውም፤ በመጠባበቂያ ስፍራዎች ሁሉ ተቀመጡላቸው፤ ተፀፅተው ከተመለሱ፣ ሰላትንም ካዘወተሩ፣ ዘካትንም ከሰጡ መንገዳቸውን ልቀቁላቸው፤ አላህ እጅግ መሃሪ፣ አዛኝ ነውና!"[8] ብዙዎች ይህን አንቀጽ ኢስላም ተከታዮቹን በሌሎች ላይ እንደሚያነሳሳና ፅንፈኝነትንም እንደሚሰብክ ለመሞገት ይጠቅሱታል። ይህ እሳቤ ስህተት መሆኑ እንደሚከተለው ባጭሩ ይብራራል፡-*

*አንቀፁ በውስን ታሪካዊ ሂደት መሃል የሚገጥም እንጂ የሁልጊዜ መርሆን የሚያስተላልፍ አይደለም። በስምንተኛው አመተ-ሂጅራ የአላህ ነብይ የተሰደዱበትን የትውልድ አገራቸውን መካ መልሰው ከተቆጣጠሩ በኋላ እዚያ የነበሩ ከፊል ጣኦት አምላኪያንን አስመልክቶ የተላለፈ መመሪያ ነው። የመካ ጣኦት አምላኪያን*

ብለው ስለሞገቱ አይደለም። ይህ ሚዛን ለኢስላማዊ የሽብር ቡድኖችም ይሰራል። ለዚያም ነው ሸይኹ የISIS እና ሌሎች የሽብር ቡድኖች ማንነት ከውስጥ አዋቂው በስተቀር እውነቱን ሊያውቅ የሚችል የለም ያሉት።

[8] አት-ተውባህ 9፡ 5

*ሁለት አይነት ነበሩ፤ ከፊሎቹ ከመልእክተኛው ጋር የፈፀሙትን የሰላም ስምምነት*[9] *ጠብቀው ያቆዩ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ቃል ኪዳናቸውን አፍርሰው ሙስሊሞችንና ሌሎች በስምምነቱ ላይ የተሳተፉ ወገኖችን የተዋጉ ነበሩ። ቃልኪዳናቸውን ያከበሩትን አስመልክቶ በዚያው ምእራፍ ላይ የሰላም ስምምነቱ እንዲጠበቅላቸው በአፅኖት ያዛል።*

*ከላይ ከጠቀስነው አንቀፅ በፊት ባለው አንቀፅ (በቁጥር 4) ላይ እንዲህ ይላል፦"ከአጋሪዎቹ ቃል የተጋባችኋቸውና ከዚያም ምንም ያላጎደሉባችሁ፣ በናንተም ላይ አንድንም ያላገዙ ከሆኑት በስተቀር፤ ቃል ኪዳናቸውን እስከጊዜያቸው (መጨረሻ) ድረስ ሙሉላቸው፤ አላህ ጥንቁቆችን ይወዳልና።"*[10] *በአንቀፅ 7 ላይም እንዲህ ይላል፦ "..(በቃል ኪዳናቸው) እስከፀኑ ድረስ ፅኑላቸው፤ አላህ ጥንቁቆችን ይወዳልና።"*[11]

*ሆኖም ቃል ኪዳናቸውን ያፈረሱትን በተመለከተ ግን የተከበሩት ወራት ሲገባደዱ ጦርነት ታወጀባቸው፤ ይህም የሆነው እንዲሁ ጣኦት አምላኪያን ስለነበሩ ብቻ እንዳልሆነ ግልፅ ነው፤ ቃላቸውን የጠበቁት ጣኦታውያን ላይ ጦር አልተመዘዘምና! ነገር ግን ከዚያ በፊት በመካ ሙስሊሞችን ሙስሊም በመሆናቸው ብቻ ሲያሰቃዩ፣*

[9] ከሙስሊም መንግስት ጋር ቃል ኪዳን መፈፀም ማለት ግብር (ጂዚያ) እየከፈሉ በሰላም መኖር ነው። የአንድ ሀገር ዜጋ ለመንግስት ግብር እንደሚከፍለው ሁሉ ሙስሊም ያልሆኑ ዜጎች ሙስሊሞች እንደ ዜጋ የሚያወጧቸውን የተለያየ ወጪዎችና ተግባሮች የማይፈፅሙ በመሆኑ የግብር ክፍያ እንዲከፍሉ ይደረጋል። ለምሳሌ ሙስሊሞች አካባቢያቸውን ከጥቃት የመጠበቅ ግደታ ሲኖርባቸው የቃል ኪዳን ነዋሪ ህዝቦች ግን አይጠበቅባቸውም። ሆኖም ማንም እነርሱን እንዳያጠቃ ለደንነታቸው ግብር ይከፍላሉ። መንግስት ደግሞ የእነርሱን ደህንነት የማስጠበቅ ግደታ አለበት። በተመሳሳይ ሙስሊሞች ለድሀ የሚከፋፈል የዘካ ግደታ ሲኖርባቸው የቃል ኪዳን ነዋሪዎቹ ግን ከዚህ ግደታ ውጭ ናቸው። የተወሰነ ቢለያይም ተመሳሳይ የክፍያ ሁኔታ በመፅሀፍ ቅዱስም አለ።

[10] አት-ተውባህ 9:4

[11] አት-ተውባህ 9:7

*ሲዘርፉና ሲገድሉ የነበሩ፣ መልዕክተኛውንና ባልደረቦቻቸውን ከትውልድ አገራቸው ያፈናቀሉ፣ በተለያዩ አጋጣሚዎች ነብዩን ለመግደል የሞከሩ፣ ሙስሊሞች ወደ ተሰደዱበት አገር ድረስ በተደጋጋሚ ጦር ሰብቀው በመዝመት ሊያጠፏቸው የጣሩ፣ ቃል ኪዳናቸውንም ያፈረሱና ለማፍረስም ወደኋላ የማይሉ ከዳተኞች ነበሩ። ይህንን እውነታ አንቀፅ ቁጥር 8 ላይ ሲያመላክት እንዲህ ይላል፦"በናንተ ላይ ቢያይሉ ስለናንተ አምላክንም (ወይም "ዝምድናንም") ሆነ ቃልኪዳንን (ወይም "ከለላን") የማይጠብቁ ሆነው ሳለ እንዴት (ቃልኪዳን ይኖራቸዋል)?"[12] በአንቀፅ 13 ላይም እንዲህ ይላል፦ "መሃላዎቻቸውን ያፈረሱትንና መልእክተኛውን ለማስወጣት የፈለጉትን ህዝቦች እነርሱ መጀመሪያ ላይ (መዋጋት) የጀመሯችሁ ሆነው ሳለአትጋደሏቸውምን?.." [13] የጦር ትንኮሳውን የጀመሩት ከሃዲያኑ ራሳቸው መሆናቸው እንደተወሳ ያስተውሉ!*

*እናም በጥቅሉ አንዳንዶች እንደሚያደርጉት አንቀፅ ቁጥር 5ን ቆንጥሮ "ቁርኣን ሙስሊም ያልሆነ ሁሉ እንዲገደል ያዛል" ሲሉ መሞገት በጣሊያን ወረራ ጊዜ "ጣሊያኖችን ተዋጉ፤ ስታገኟቸውም ግደሏቸው!..» በሚል ቃል የተላለፉ የጦር ትእዛዞችን ኢትዮጵያውያን ጣሊያኖችን ጣሊያናውያን በመሆናቸው ብቻ ሁሌም የሚገድሉ ዘረኞች እንደሆኑ ለመሞገት በማስረጃነት እንደማቅረብ ነው!*

*ሆኖም በዚሁ ርዕስ ላይ ከላይ ከተብራራው አንቀፅ ጋር ተያይዞ የሚነሳ ጥያቄ አለ፤ ቁጥር 5 ላይ"ተፀፅተው ከተመለሱ፣ ሰላትንም ካዘወተሩ፣ ዘካትንም ከሰጡ መንገዳቸውን ልቀቁላቸው.."ሲል ኢስላምን ካልተቀበሉ መገደላቸው ብይኑ*

[12] አት-ተውባህ 9:8

[13] አት-ተውባህ 9:13

*ከእምነታቸው ጋር እንጂ ቃልኪዳን ከማፍረሳቸው ጋር እንድማይያያዝ አያስገነዝብም ወይ?*

*መልሱም፦ "አያስገነዝብም" ነው! ምክንያቱም ተፀፅተው መመለሳቸውና ኢስላምን መቀበላቸው በበፊቱ ጥፋታቸው የተነሳ የተበየነባቸውን ቅጣት የሚያስምር እድል እንጂ ሌላ አይደለም። ይህንን በምሳሌ እናብራራው፦*

*አንድ በስርቆት ወንጀል ምክንያት የ5 አመት እስራት የተፈረደበት ግለሰብ ለረጅም ጊዜ ከተጠናወተው የሲጃራና የመጠጥ ሱስ ሙሉ በሙሉ ከተላቀቀ እስራቱ እንደሚሻርለት ቢነገረው እስራቱ የተፈረደበት በሱሰኝነቱ ምክንያት ነው ማለት አይደለም! ከሱሱ መላቀቁ ግን በስርቆቱ ምክንያት የተፈረደበትን ቅጣት ሊያስቀርለት የሚችል አበረታች እድል ነው።*

*በአንቀፁም ላይ አጋሪያኑ ሞት የተፈረደባቸው ቃልኪዳን በማፍረሳቸውና ሙስሊሞችን በመውጋታቸው እንጂ ሙስሊም ባለመሆናቸው ብቻ አይደለም፤ ፍርዱ ቃል ኪዳናቸውን ያከበሩትን አይመለከትምና! ከጥፋታቸው ታቅበው ኢስላምን ከተቀበሉ ግን ቅጣቱን የሚያስምር እድል ያገኛሉ ማለት ነው። ያስተውሉ!*

*ስለሆነም ሙስሊሞች እስከዛሬ ሙስሊም ያልሆነን ሁሉ የመግደል ግዴታ እንዳለባቸው ከአንቀፁ ወይም ከሌሎች የሀይማኖቱ መመሪያዎች ተገንዝበው አያውቁም! ይህ ከዚህ ውጭ ያሉ የቁርኣን ወይም የሐዲሥ ጥቅሶች መሰል ማብራሪያ እንዳላቸው የሚጠቁም ምሳሌ ይሁን። ሸይኹ'ል–ኢስላም ኢብኑ ተይሚይ–ያህ እንዲህ ይላሉ፦ "ሰዎች ከአላህ በቀር (እውነተኛ) አምላክ እንደሌለና ሙሐመድም የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውን እስኪመሰክሩ፣ እንዲሁም ሰላትንም እስኪያዘወትሩና ዘካትንም እስኪሰጡ ደረስ እንድጋደላቸው ታዝዣለሁ" በሚለው የነብዩ ንግግር ላይ ፍላጎታቸው እነዚያ ሊጋደሏቸው አላህ የፈቀደ የሆኑት ተዋጊ*

*ጠላቶችን ነው፤ ቃላቸው እንዲሞላ አላህ ያዘዘ የሆኑትን ቃል ኪዳነኞችን ፈልገው አይደለም.."*[14]

*አዎን! ሙስሊሞች የሚከተለውን የአላህ መልዕክተኛ ንግግር ያከብራሉ፦ "(የሰላም) ቃል ኪዳን የተገባለትን የገደለ የጀነትን ሽታ እንኳ አያሸትም፤ የርሷ ሽታ የአርባ አመታት የጉዞ ርቀት ላይ ይገኛል!"*[15] *ይህ ሙስሊም ያልሆኑ የሰላም ቃልኪዳን ባለቤቶችን መግደልን የሚያወግዝ ቃል ነው።*[16] *የዘመናችን የኢስላም ሊቃውንት "የቃልኪዳን ባለቤቶች" የሚለው ገለፃ በሙስሊሞች አስተዳደር ስር የሚኖሩ ሙስሊም ያልሆኑ ወገኖችን፣ ህጋዊ ቪዛ ይዘው ወደ ሙስሊሞች አገራት የገቡትንና ሌሎች ባለ ቃልኪዳኖችን ሁሉ እንደሚያካትት ያስረዳሉ።*[17]

*እንዲያውም በተለያዩ ጥፋቶች የተነሳ ሞት የተገባው ውስን ግለሰብ ቢኖር እንኳ የፍርዱ ተፈፃሚነት በግለሰቦች ወይም በጭፍራዎች እጅ እንዳልሆነ የታወቀ ነው።*

---

[14] መጅሙዑ'ል-ፈታዋ 19/20

[15] አል-ቡኻሪይ ቁ. 3166 ከአብዱ'ላህ ኢብኑ ዐምር ዘግበውታል

[16] ነቢዩ ሙሀመድ በንግግር ብቻ ሳይሆን በተግባርም ከቃል ኪዳን ባለቤቶች ህግጋቱን የጠበቀ ግንኙነት ነበራቸው።"ነብዩ ﷺ በእርሳቸው ዘመን ከነበሩት ከሀዲዎች ጋር ንግድ ይነግዱ ነበር። ከእነርሱም ይገዛሉ ፣ ይሸጣሉ። ይህ በሰዎች መካከል የሚገኝ ጥቅም ነው። እንዲሁም ከእነርሱ ምሁራኖች እውቀት በመውሰድ መጠቀም ይቻላል። ምክንያቱም ነብዩ ﷺ ከመካ ወደመዲና ተሰደው በሄዱ ጊዜ አቅጣጫ የሚያሳያቸው ዓብደላህ ብን ዑረይቂጥ አልለይሲ የተባለን ካፊር ቀጥረዋል። (ቡኻሪ፡ 2263)"(ሙስሊም ካልሆኑ ሰዎች ጋር በሚኖረን ግንኙነት ላይ ሸሪዓዊ ህግጋቱ፡ ትርጉም ዩሱፍ አህመድ፡ ገፅ 17)

[17] ሸይኽ ፈውዛን (አላህ ይጠብቃቸው) እንዲህ ብለዋል"ልክ እንደዚሁ ወደአገራችን በእኛ ቃልኪዳን ስር የሚገቡ ከሀዲያን ላይ ድንበር አንተላለፍም። አንድ ሰው በእነርሱ ላይ ድንበር ቢያልፍ እንዲሁ አንተወውም። ወደአገራችን የገባው ከሀዲ ወደአገሩ በሰላም እስኪመለስ ድረስ አንድም ሰው ሊተናኮለው ወይም ሊያሰቃየው አይገባም። ምክንያቱም እኛ ነን በቃል ኪዳን እንዲገባ ያደረግነው። እኛ ነን የሰላሙን ዋስትና የሰጠነው። ለእርሱ ሐቁን መሙላት ግድ ይሆንብናል። ምክንያቱም ኢስላም የተንኮል፣ ቃልኪዳንን የማፍረስ፣ ድንበር የመተላለፍ፣ ከሀዲዎች ወደኢስላም እንዳይገቡ የሚከለክል እምነት አይደለም። ሙስሊሞች ከከሀዲዎች ጋር ባላቸው ግንኙነት መልካም ሊሆኑ ይገባል። ይህ ከሆነ እምነቱን ይፈልጉታል፣ የኢስላምን ፍትሀዊነት በቀላሉ ይደርሱበታል። አላህ በከሀዲዎች ላይ ድንበር መተላለፍን ከልክሏል።"(ሙስሊም ካልሆኑ ሰዎች ጋር በሚኖረን ግንኙነት ላይ ሸሪዓዊ ህግጋቱ፡ ትርጉም ዩሱፍ አህመድ፡ ገፅ 17)

*አዎን! ኢስላም መንፈሳዊ ብቻ ሳይሆን ሁለንተናዊ የህይወት መንገድ በመሆኑ በተለያዩ ጥፋቶች ላይ የራሱን ቅጣቶች ይበይናል። እነዚህ ብይኖች ተግባራዊ የሚሆኑት ግን በመንግስት ደረጃ ነው[18]፤ ይህም ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸውና ቅጣቱ እንዳይተገበር የሚያግዱ ምክንያቶች መወገዳቸው በፍርድ ቤት ከተጣራ በኋላ እንጂ በዘፈቀደ አይደለም! ይህ በአለማዊ ህገ-መንግስታት ላይም የፀደቀ ነው፤ አንድ ወንጀለኛ በሌለበት የሞት ፍርድ ቢወሰንበት የተደበቀበትን ቦታ ያወቀ ግለሰብ ምናልባት ለፖሊስ ይጠቁም ይሆናል እንጂ ፍርዱን ለመተግበር ራሱ ቢገድለው እርሱ ራሱ በነፍሰ ገዳይነት እንደሚከሰስ ግልጽ ነው! ጭራሽ ያለተፈረደበትን መግደል ደግሞ የከፋ ነው። እንዲህ አይነቱ ሂደት ስርዓት አልበኝነትን ያወርሳልና! ኢስላም ደግሞ ከሌሎች ይበልጥ ስርዓት አልበኝነትን እንደሚዋጋ ህግጋቱ ሁሉ ይመሰክራሉ![19]*

[18] እንደ ISIS፣ አልቃኢዳ፣ ቦኩሀራም ያሉና መሰል የሽብር ቡድኖች የተያያዙትን የሽብር ተግባር ኢስላማዊ ለማስመሰል ከኢስላማዊ ትውፊት (ቁርአን፣ ሀዲስ እና የሙህራን ንግግሮችን) ቢያጣቅሱም ተግባራቸው ኢስላማዊ አለመሆኑን የሚያሳይልን ትልቁ ልዩነት ኢስላማዊው ጂሀድ የሙስሊሞች መሪ ከተመሰከረላቸው (እውቅና ካላቸው) የሙስሊም ምሁራን ጋር በመመካከር በቁርአንና በሀዲስ የተቀመጡ ለጂሀድ መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች መሟላታቸው ተረጋግጦና ከልካይ ነገሮች መወገዳቸው ተጠንቶ፣ የጂሀዱ ጥቅምና ጉዳት ተሰልቶ በመንግስት ደረጃ የሚታወጅ፤ እያንዳንዱ ሒደትም በቁርአንን በሀዲስ እየተመዘነ የሚመራ ነው። ከዚህ ውጭ ያለው ራሱን በሙስሊም ስም ያደራጀ ሁሉ ቁርአንና ሀድስ ብሎም የዑለሞችን ንግግር ስላጣቀሰ ብቻ የሽብር ድርጊቱ ኢስላማዊ ነው ማለት አይደለም። የእምነትና ተግባር መግጠም እንጂ ስምና ጥቅስ ሙስሊም (ኢስላማዊ) አያደርግም። አንድ ሰው ሙስሊም ነው የሚባለው ቁርአንና ሀዲስን ስለጠቀሰ ወይም ስሙ የሙስሊም ስለሆነ ሳይሆን በቁርአንና ሀዲስ የተቀመጡ የአምልኮ ተግባራትን ነቢዩ ባስተማሩትና ሙስሊሞች በሚተገብሩት መልኩ ሲተገብር ብቻ ነው። ጂሐድም ተመሳሳይ ነው።

[19] አምላካችን አላህ የቃል ኪዳን ባለቤቶችን ግድያ ከሙስሊም ግድያ ነጥሎ አያየውም። በተከበረ ቃሉም"ለምእመንም በስሕተት ካልኾነ በቀር ምእመንን መግደል አይገባውም። ምእመንንም በስህተት የገደለ ሰው ያመነችን ጫንቃ (ባሪያ) ነጻ ማውጣትና ወደ ቤተሰቦቹም የምትሰጥ ጉማ ምሕረት ካላደረጉለት በስተቀር (መክፈል) አለበት፡፡ እርሱ (ተገዳዩ) ምእመን ሲኾን ለእናንተ ጠላት ከኾኑትም ሕዝቦች ቢኾን ያመነችን ጫንቃ ነጻ ማውጣት (ብቻ) አለበት፡፡ በእናንተና በእነሱ መካከል ቃል ኪዳን ካላቸውም ሕዝቦች ቢኾን ወደ ቤተሰቦቹ በእጅ የምትሰጥ ጉማና ያመነችን ጫንቃ ነጻ ማውጣት አለበት፡፡ ያላገኘ ሰውም ተከታታዮችን ሁለት ወሮች መጾም አለበት፡፡ አላህ መጸጸትን ለመቀበል (ደነገገላችሁ)፡፡ አላህም ዐዋቂ ጥበበኛ ነው፡፡"(አን-ኒሳእ 4:92) በማለት በስህተት የተገደለን የቃል ኪዳን ባለቤት በስህተት ከተገደ ሙስሊም ጋር እኩል አድርጎታል።

# በጣትህ ስትጠቁም፤ ሶስቱ ወደ አንተ ነው!

*ታዲያ በኢስላም ከተለያዩ መስፈርቶችና ሂደቶች በኋላ በመንግስት ደረጃ የሚታወጅ ጦርነት ላይ ራሱ ሊከበሩ የሚገቡ የፍትህ ወሰኖች አሉ። ይህንን ከማውሳታችን በፊት ግን ስለ ኢስላም "ደመኝነት" ዘወትር ለሚለፍፉ አንዳንድ ፀሃፊዎች ለንፅፅር ያህል ከብሉይ ኪዳን የሚገኙ ጥቅሶችን ላስታውስ እወዳለሁ!*

***1***–*"የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እስራኤል ከግብፅ በወጣ ጊዜ አማሌቅ በመንገድ እየተቃወመ ያደረገበትን እበቀላለሁ። አሁንም ሄደህ አማሌቅን ምታ፣ ያላቸውንም ሁሉ ፈጽመህ አጥፋ፣ አትማራቸውም፤ ወንዱንና ሴቱን ብላቴናውንና ህጻኑን በሬውንና በጉን ግመሉንና አህያውን ግደል።"*[20]

*የሚደንቀው እንደታዘዙት ህዝቡን ሁሉ ካጠፉ በኋላ ለንጉሱ፣ ለአንዳንድ የቤት እንስሶችና መልካም ንብረቶች በመራራታቸው ትዕዛዙን እንዳልፈፀሙ ተቆጥሮ ከንግስና ተወግደዋል። ከአንቀፅ 8 እስከ 11 እንደሚከተለው ይነበባል፦"የአማሌቅንም ንጉስ አጋግን በሕይወቱ ማረከው፥ ሕዝቡንም ሁሉ በሰይፍ ስለት ፈጽሞ አጠፋቸው። ነገር ግን ሳኦልና ሕዝቡ ለአጋግ፥ ለተመረጡትም በጎችና በሬዎች፥ ለሰቡትም ጥጆችና ጠቦቶች፥ ለመልካሞቹም ሁሉ ራሩላቸው፥ ፈጽሞ ሊያጠፏቸውም አልወደዱም፤ ነገር ግን ምናምንቴንና የተናቀውን ሁሉ ፈጽመው አጠፉት። የእግዚአብሔርም ቃል፦ ሳኦል እኔን ከመከተል ተመልሶአልና፥ ትእዛዜንም አልፈጸመምና ስላነገስሁት ተጸጸትሁ ብሎ ወደ ሳሙኤል መጣ።.."*

[20] መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 15:2-3

*2-"እግዚአብሔርም፦ ሴዎንንና ምድሩን በእጅህ አሳልፌ መስጠት፥ እነሆ ጀመርሁ፤ ምድሩን ትገዛት ዘንድ መውረስ ጀምር፤ አለኝ። ሴዎንም ሕዝቡም ሁሉ ሊጋጠሙን ወደ ያሀጽ ወጡ። አምላካችንም እግዚአብሔር እርሱን አሳልፎ ሰጠን፤ እርሱንም ልጆቹንም ሕዝቡንም ሁሉ መታን። በዚያን ጊዜም ከተሞቹን ሁሉ ወሰድን የተቀመጡባቸውንም ሰዎች ሁሉ ሴቶችንም ሕፃናቶችንም አጠፋን፤ አንዳችም አላስቀረንም!"* [21]

*3-"ነገር ግን አምላክህ እግዚአብሔር ርስት አድርጎ ከሚሰጥህ ከእነዚህ አሕዛብ ከተሞች ምንም ነፍስ አታድንም። ነገር ግን ለአማልክቶቻቸው ያደረጉትን ርኵሰት ሁሉ ታደርጉ ዘንድ እንዳያስተምሩአችሁ፥ በአምላካችሁም በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት እንዳትሠሩ፥ አምላክህ እግዚአብሔር እንዳዘዘህ ኬጢያዊውን አሞራዊውንም ከነዓናዊውንም ፌርዛዊውንም ኤዊያዊውንም ኢያቡሳዊውንም ፈጽመህ ታጠፋቸዋለህ።"*[22]

*4-"በከተማይቱም የነበሩትን ሁሉ፥ ወንዱንና ሴቱን፥ ሕፃኑንና ሽማግሌውን፥ በሬውንም በጉንም አህያውንም፥ በሰይፍ ስለት ፈጽመው አጠፉ።"*[23]

*5-"እግዚአብሔርም፦ በከተማይቱ በኢየሩሳሌም መካከል እለፍ፥ በመካከልዋም ስለ ተሠራው ርኵሰት ሁሉ በሚያለቅሱና በሚተክዙ ሰዎች ግምባር ላይ ምልክት ጻፍ አለው። እኔም እየሰማሁ ለሌሎቹ። እርሱን ተከትላችሁ በከተማይቱ መካከል እለፉ ግደሉም፤ ዓይናችሁ አይራራ አትዘኑም፤ ሽማግሌውንና ጐበዙን ቈንጆይቱንም ሕፃናቶቹንና ሴቶቹን ፈጽማችሁ ግደሉ፤ ነገር ግን ምልክቱ ወዳለበት ሰው ሁሉ*

[21] ኦሪት ዘዳግም 2:31-34

[22] ኦሪት ዘዳግም 20፡ 16-18

[23] መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ 6:21

*አትቅረቡ፤ በመቅደሴም ጀምሩ አላቸው። በቤቱም አንጻር ባሉ ሽማግሌዎች ጀመሩ። እርሱም፦ ቤቱን አርክሱ፥ በተገደሉትም ሰዎች አደባባዮችን ሙሉ፤ ውጡ አላቸው። እነርሱም ወጥተው በከተማይቱ ገደሉ።"*[24]

6-"*የእስራኤልንም አምላክ እግዚአብሔርን የማይፈልግ ታናሽ ወይም ታላቅ፣ ወንድ ወይም ሴት ቢሆን ይገደል ዘንድ ማሉ።"*[25]

7-"*አንቺ ወራዳ የባቢሎን ልጅ ሆይ! ስለተበቀልሽን የሚበቀልሽ የተመሰገነ ነው። ሕፃናቶችሽን ይዞ በአለት ላይ የሚፈጠፍጣቸውየተመሰገነ ነው።"*[26]

8-"*ሰማርያ በአምላክዋ ላይ ዐምፃለችና በደልዋን ትሸከማለች፤ በሰይፍ ይወድቃሉ፥ ሕፃኖቻቸውም ይፈጠፈጣሉ፥ እርጉዞቻቸውም ይቀደዳሉ።"*[27]

9-"*እርም የሆነውም ነገር የተገኘበት ሰው የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን አፍርሶአልና፥ በእስራኤልም ዘንድ በደል አድርጎአልና እርሱና ያለው ሁሉ በእሳት ይቃጠላሉ።"*[28]

*ጥቅሶቹን ያሰፈርኩት አንዳንዶች ቁርኣን አግባብ የሌለው ግድያን እንደሚያነሳሳ ሲሞግቱ እነርሱ የሚያምኑበት "መፅሐፍ ቅዱስ" ደግሞ ከማነሳሳት አልፎ ሙሉ የጅምላ ጭፍጨፋን የሚያፀድቅ እንደሚሆን ለማሳየት ብቻ ነው። የስነ ታሪክና ሀይማኖቶች ጥናት ተመራማሪ የሆነው አሜሪካዊው ዝነኛ ፕሮፌሰር ፊሊፕ*

[24] ትንቢተ ሕዝቅኤል 9:4-7

[25] መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ 15:13

[26] መዝሙር ዳዊት 137:8-9

[27] ትንቢተ ሆሴዕ 13:16

[28] መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ 7:15

*ጄንኪንስ (Philip Jenkins) እ. ኤ. አ. በ March 8, 2009 "Dark Passages" በሚል አርዕስት ስር ባስነበበው መጣጥፍ ላይ የሚከተለውን ምስክርነት ይሰጣል፦ "..In fact, the Bible overflows with"texts of terror,"to borrow a phrase coined by the American theologian Phyllis Trible. The Bible contains far more verses praising or urging bloodshed than does the Koran, and biblical violence is often far more extreme, and marked by more indiscriminate savagery. The Koran often urges believers to fight, yet it also commands that enemies be shown mercy when they surrender. Some frightful portions of the Bible, by contrast, go much further in ordering the total extermination of enemies, of whole families and races - of men, women, and children, and even their livestock, with no quarter granted..."*

*ትርጉሙም፦"በተጨባጭ መፅሐፍ ቅዱስ - በአሜሪካዊቷ የመንፈሳዊ ጥናቶች ምሁር ፊሊስ ትሪብል የተከሸነ ሀረግን ለመዋስ ያህል– "በሽብር ጥቅሶች" የተጥለቀለቀ ነው! መፅሐፍ ቅዱስ ቁርኣን ከሚያካትታቸው (የግድያ አንቀፆች) በሰፊው የበዙ ደም ማፍሰስን የሚያወድሱና የሚያነሳሱ አንቀፆችን አካትቷል! መፅሐፍ ቅዱሳዊው ደመኝነት ባብዛኛው እጅግ የከፋ ፅንፈኝነት ያለው ሲሆን ይበልጡኑ በጅምላ ጭፍጨፋ የሚገለፅ ነው። ቁርኣን በብዙ አጋጣሚዎች አማኞችን ወደ ትግል ይገፋፋል፤ ከመሆኑም ጋራ ጠላቶች ሲማረኩ አዘኔታ እንዲቸሩ ያዛል። በአንፃሩ ግን አንዳንድ አስፈሪ የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ጠላትን፣ ከነሙሉ ቤተሰቦችንና ዘሮች፣ ወንዶችን፣ ሴቶችን፣ ህፃናትን፣ ከብቶቻቸውን*

*እንኳ ሳይቀር ያለምንም መፈናፈኛ በጅምላ በማጥፋት ረገድ እጅግ ርቀው ይሄዳሉ።."*[29]

*ፕሮፌሰር ፊሊፕ ጀንኪንስ በ2010 ከ National Public Radio ጋር ባደረገው ቃለ ምልልስ ይህን እምነቱን አጽንቷል። በ 2011 ባሳተመው "Laying Down The Sword: Why We Can't Ignore The Bible's Violent Verses" በተሰኘው መጽሀፉ ደግሞ ይህንን ድምዳሜውን በሰፊው አብራርቷል። ይህ ምሁር ክርስቲያን እንጂ ሙስሊም አይደለም።*[30]

*አንዳንዶች "እነዚህ ያለፉ ታሪካዊ ክስተቶች ናቸው፤ ቁርኣን ላይ ያሉት ግን ለአማኞች የተላለፉ መመሪያዎች ናቸው!" ይሉ ይሆናል። ይህ ሙግት ግን ነገሩን ያብሰዋል፤ ምክንያቱም አብዛኛዎቹ የመፅሐፍ ቅዱስ አንቀፆች ላይ እንደምናስተውለው ጭፍጨፋዎቹ በአምላክ የታዘዙና በነብያት የተፈፀሙ ናቸው! ያልሆኑትም ያለ አንዳች ተቃውሞ ፀድቀዋል፤ ስለዚህ ተፈፃሚነታቸው ገደብ ስለሌለው በቀጥታ በተጨባጩ ዓለም ላይ ተተግብረዋል!*[31] *በቁርኣን ላይ ያሉ*

[29] ሙሉ መጣጥፉን እዚህ ያገኙታል፦
http://www.boston.com/bostonglobe/ideas/articles/2009/03/08/dark_passages/?page=full

[30] ስለግለሰቡ ማንነት የሚከተለው የዊኪፒዲያ ሊንክ ላይ ማንበብ ይችላሉ፦
http://en.wikipedia.org/wiki/Philip_Jenkins

[31] ክርስቲያን ሊቃውንት የብሉይ ኪዳን ህጎችን የማህበራዊ (civil/social)፣ የክብረ በዓላዊ (ceremonial/religious) እንድሁም የግብረ-ገባዊ (moral/ethical) በማለት በሶስት ይከፍሏቸዋል። (ከአንድ በላይ ጋብቻ፡ ንፅፅራዊ አቀራረብ፡ ዐቅበተ ኢስላም ኑረዲን፡ ገፅ 192) በዚህ ክፍልፋይ መሰረት ክርስቲያን ሊቃውንት ተሽረዋል የሚሏቸው ህጎች ከክብረ በዓላት ጋር ተያይዘው ያሉትን ሲሆን የጦርነት ህጎች ደግሞ ከማህበራዊ (civil) ህጎች የሚመደቡ ናቸው። የማህበራዊ (አስተዳደራዊ) ህጎች ክርስቲያን ነገስታት ህዝቦችን ሲያስተዳድሩ የሚያስተዳድሩባቸው ህጎች በመሆናቸው ፈፅመው ሊሻሩ የማይችሉ ናቸው። በመሆኑም በመቼም ጊዜ የሚያስተዳድር ክርስቲያን ንጉስ ለሚገጥመው ጦርነት ሊከተላቸው የሚገቡ ህጎች በመሆናቸው የጦርነት ህጎች ሊሻሩ አይችሉም።

*የጂሃድ አንቀፆች ግን የተለያዩ ገደቦች እንዳሏቸው ሙስሊሞች ሁሉ ስለሚረዱ በአንድም አጋጣሚ አንድም በኢስላማዊ መንግስት የሚመራ ጦር ህዝቦችን በጅምላ ጭፍጨፋ አጥፍቶ አያውቅም! በየትኛው የኢስላም ማህደር ላይ ነው ጭራሽ የማይዋጉ ወንዶች፣ ሴቶች፣ አዛውንት፣ ህፃናት፣ እንስሳት የተገደሉት?! በየትኛው መዝገብ ላይ ሰፍሯል?!*

*መቼም ይህን ሁሉ የዘረዘርኩት "ክርስቲያኖች ደመኞች ናቸው!" ብዬ አስቤ እንዳልሆነ ግልፅ ነው፤ እምነቱና ሰበካውም በአብዛኛው ሽብርን የሚያበረታታ አይደለም።*[32] *ታዲያ እናንተ አጃችሁን ወደ ቁርኣን የቀሰራችሁ ክርስቲያን ግለሰቦች ሆይ! ለነዚያ አንቀፆቻችሁ ማብራሪያ ካላችሁ እኛ ደግሞ ስለምትመዟቸው ቁርኣናዊ አንቀጾቻችን የተሻለና ይበልጥ የተቃና ማብራሪያ እንዳለን ማወቅ ተሳናችሁን?!*

## የጂሐድ ህግጋት

*አሁን የላይኞቹን አንቀፆች ከሚከተሉት ኢስላማዊ የጦርነት ህጎች ጋር አነፃፅሩልኝ!*

***የኛ ኢስላም፡-*** *የሙስሊሙን ህልውና ለመፋቅ ሰይፋቸውን ከመዘዙ ጠላቶች ጋር በሚደረግ የጦር ሜዳ ፍልሚያ ላይ እንኳ ወሰን ማለፍን የሚከለክል ነው! አላህ እንዲህ ብሏል፡-"እነዚያ የሚጋደሏችሁን በአላህ መንገድ ላይ ተጋደሏቸው፤ ወሰንም አትለፉ፤ አላህ ወሰን አላፊዎችን አይወድምና።"*[33]

[32] ሆኖም እነዚህን የመፅሀፍ ቅዱስ ጥቅሶች የሚያጣቅሱ በርካታ ክርስቲያን የሽብር ቡድኖች እንዳሉ መታዎቅ አለበት። ፖለቲካዊ አላማ ያላቸው ሁሉ ሙስሊሙን ለማሸማቀቅ ሽብርተኝነትንና ፅንፈኝነትን የሙስሊም መገለጫ አድርገው ስለውት እንጂ እጅግ በጣም በርካታ ክርስቲያን የሽብር ቡድኖች በርካታ ጥፋቶችን አካሄደዋል፤ እያካሄዱ ይገኛሉ። ለምሳሌ Army of God፣ Ku Klux Klan፣ Lord's resistance army ተጠቃሽ ናቸው። በመንግስት ደረጃም የመስቀል ጦርነት፣ ቅኝ ግዛትና የአውሮፓው የኃይማኖት ጦርነት ሁሉም ሀይማኖታዊ መሰረት ያላቸው"የሽብር"ድርጊቶች ናቸው።

[33] አል-በቀረህ 2: 190

*አዎን! “ለሚጋደሏችሁ አንገታችሁን ስጡ!” አልተባልንም! ግን ራስን በመከላከል ሂደትም ቢሆን የትኛውንም የፍትህና የሰብዓዊነት ወሰን ማለፍን ተከልክለናል! “ወሰንም አትለፉ!” የሚለውን የአንቀፁን መልዕክት ታዋቂው የመልዕክተኛው ባልደረባ ዐብዱ’ላህ ኢብኑ ዐብ-ባስ ሲያብራሩ እንዲህ ብለዋል፦ ”ሴቶችን፣ ህፃናትን፣ አዛውንትን፣ እርቅን ወደናንተ ያቀረበንና እጁን የሰበሰበንም አትግደሉ! ይህን ካደረጋችሁ ወሰን አልፋችኋል!” ማለቱ ነው!"*[34] *ያስተውሉ! ይህ ሁሉ ገደብ በጦርነት ላይ ነው።*

*እንዲሁም ነብያችን ዘማቾችን ለውጊያ በሚልኩበት አጋጣሚ ዘወትር ከሚመክሯቸው ምክሮች መካከል፦ "ቃል ኪዳን አታፍርሱ፤ ሬሳንም አትቆራርጡ፤ ህፃንም አትግደሉ*[35] *.." የሚል አደራ ይገኝበታል።*[36] *ዐብዱ’ላህ ኢብኑ ዑመር የሚከተለውን አስተላልፈዋል፦ "በመልዕክተኛው አንድ ዘመቻ ላይ አንዲት የተገደለች ሴት ተገኘች፤ እርሳቸውም ሴቶችንና ህፃናትን መግደልን አወገዙ።"*[37] *አል-ኢማም ኢብኑ ዐብዲ’ል-በር ይህንን ዘገባ ባብራሩበት አጋጣሚ እንዲህ ብለዋል፦ "የኢስላም ሊቃውንት የዚህን ሐዲሥ ጥቅል መልዕክት በመቀበል ላይ ተስማምተዋል፦ እናም እነርሱ ዘንድ የተዋጊ ጠላቶችን ሴቶችና ህፃናትን መግደል*

---

[34] አጥ-ጠበሪ - “ጃሚዑ’ል-በያን..” (“ተፍሲሩ’ጥ-ጠበሪ”) (3/563)፣ ኢብኑ አቢ ሓቲም - “አት-ተፍሲር” ( 1/325) ቁጥር 1721

[35] አስወድ ብን ሰሪዕ የሚከተለውን ሐዲስ አስተላልፈዋል፦ “ህጻናትን በመግደል ላይ ምንድን ነው ያነሳሳችሁ?” በማለት ጠየቋቸው። “የአላህ መልእክተኛ ሆይ! የሙሽሪክ ልጆች ስለነበሩ ነው” በማለት ምላሽ ሰጧቸው።“ምርጥ (ሶሃቦቻችሁ) የሙሽሪክ ልጆች አልነበሩምን? ፣ የሙሐመድ ነፍስ በእጁ በሆነው ጌታ እምላለሁ -አንደበቷ ስለርሷ ግልጽ እስከሚያደርግ ድረስ- አንድም ነፍስ አትወለድም ፣ በተፈጥሮ እምነቷ ቢሆን እንጅ።” (አህመድ 15589፡ ሐዲሱን አልባኒ ሶሂህ ብለውታል ሶሂህ አልጃሚዕ፡ 5571)

[36] ሙስሊም የዘገቡትና ቡረይደህ ያስተላለፉት ሐዲሥ ነው፤ ሰሑሑ ሙስሊም - ቁጥር (1731)

[37] አል-ቡኻሪይ - ቁጥር (3014) ፤ ሙስሊም - ቁጥር (1744)

*አይፈቀድም.."*[38] *በተመሳሳይ መልኩ አል-ኢማም አን-ነወዊ እንዲህ ብለዋል፦ "ይህ ሐዲሥ የሚተገበር ስለመሆኑና ሴቶችና ህፃናትም እስካልተጋደሉ ድረስ እነርሱን መግደል እርም ስለመሆኑ ሊቃውንት ተስማምተዋል.."*[39]

*እንዲሁም አነሰ ኢብኑ ማሊክ እንዳስተላለፉት ነብያችን እንዲህ ብለዋል፦ "በአላህ ስም፣ በአላህ ታግዛችሁ በመልዕክተኛው መንገድ ላይ ጉዞ ጀምሩ፤ ያረጀ ሽማግሌን፣ ህፃንን፣ (ያልደረሰ) ልጅንና ሴትን አትግደሉ! .."*[40] *እንዲሁም ረባሕ ኢብኑ አር-ረቢዕ ባስተላለፉት ዘገባ ደግሞ ነብያችን እንዲህም ብለዋል፦ "..ልጆችንና ተቀጣሪ ሰራተኛን አትግደሉ!"*[41] *እንዲሁም ከመልዕክተኛው ህልፈት በኋላ የመጀመሪያው የሙስሊሞች መሪ የሆኑት ታላቁ ኸሊፋ አቡ በክር አስ-ሲድ-ዲቅ በአንድ አጋጣሚ የዚድ ኢብኑ አቢ ሱፍያንን ለዘመቻ ሲልኩት እንደሚከተው እንደመከሩት ተዘግቧል፦ "..አስር ነገሮችን አደራ እልሃለሁ፦ ሴትን፣ ህፃንንም፣ ያረጀ ሽማግሌንም እንዳትገድል፤ የሚያፈራ ዛፍን እንዳትቆርጥ፤ ግንባታዎችን እንዳታፈራርስ፤ በግን፣ ፍየልንና ግመልን በአግባቡ ለመብላት ካልሆነ በቀር እንዳታቆስል፤ የተምር ዘንባባን (አንዳንድ መዛግብት ላይ፦ የንብ ቀፎን..) እንዳታቃጥል፤ በውሃም እንዳታሰምጠው፤ የምርኮ ንብረትንም ሳይከፋፈል እንዳትወስድ፤ እንዳትፈራም!"*[42] *አል-ኢማም አል-አውዛዒይ ይህን አስመልክቶ የሚከተለውን ብለዋል፦ "አቡ በክር አስ-ሲድ-ዲቅ የሚያፈራ ዛፍን እንዳይቆርጥና*

[38] ኢብኑ ዐድቢ'ልዐበር - "አት-ተምሂድ" (16/138)

[39] አን-ነወዊ - "ሸርሑ ሰሒሂ ሙስሊም" (12/48)

[40] አቡ ዳዉድ - ቁጥር (2614)

[41] አሕመድ - ቁጥር (15992) ፤ አቡ ዳዉድ (2669)

[42] አል-ኢማም ማሊክ - በ"አል-ሙወጥ-ጠእ" ቁጥር (1627) ላይ ከየሕያ ኢብን ሰዒድ አስተላልፈውታል፤ የዘገባው ሰነድ የተቋረጠ ቢሆንም በሌሎች ደጋፊ ምክንያቶች ይጠናከራል።

*መኖሪያ ግንባታን እንዳያፈራርስ [የዚድን] ከልክለዋል፤ ሙስሊሞችም ከርሳቸው በኋላ ይህንን (መመሪያ) ተግብረዋል።"*[43]/[44]

*በተጨማሪም ለምርኮኞች ማዘንና በጎ መዋል የጀነት ወራሾች መገለጫ ሆኖ ተወስቷል*[45]*:-"ምግብንም ከመውደዳቸው ጋር ድሃን፣ የቲምንና ምርኮኛን ያበላሉ።"*[46]

---

43 ሱነኑ'ት-ቲርሚዚይ - አብዋቡ'ስ-ሲየር - ከቁጥር 1552 ቀጥሎ የሰፈረ ነው።

44 "የጦርነት ባለቤት ያልሆኑ አካላትን የእውቀት ባለቤቶች ግልጽ አድርገዋል። እነርሱም፦ ሴቶች ፣ ህጻናቶች ፣ ሽማግሌዎች ፣ አይነ ስውራን፣ የማይድን በሽታ ያለባቸው፣ እብዶች፣ ባህታውያን፣ የገዳም ባለቤቶች (መነኩሴዎች) ናቸው። በጅሐድ ወቅት እነዚህ ሰዎች በአጠቃላይ አይገደሉም።" (ከጂሐድ ጥበብና ህግጋት ምርጥ ፍሬዎች፡ ሸይኽ አብዱረዛቅ ኢብን አብዱል ሙህሲን፡ (ትርጉም፡ ዩሱፍ አህመድ)፡ ገፅ 34)

45 ከምርከኞች አያያዝ ጋር በቀጥታ የሚገናኘው ሌላው ነጥብ ባርነት ነው። ምንም ባርነት ከነቢዩ ሙሀመድ ነቢይነት ከሺህ ዓመታት በፊት ቢጀመርም ነቢዩ ባርነትን በተለያየ መልኩ ተዋግተዋል። ከጦነት ውጪ የነበሩ የባርነት ምንጮችን አጥፍተዋል። ሆኖም ሙስሊሞች በቁጥር እጅግ አናሳ በነበሩበት፣ ከሀዲያን ከያሉበት ተሰባስበው በአንድነት እስልምናና ሙስሊሞችን የተበተነ ትቢያ ሊያደርጓቸው ቋምጠው የመጡ ከሀዲያንን አስመልክቶ አምላካችን አላህ"እነዚያንም የካዱትን (በጦር ላይ) ባገኛችሁ ጊዜ ጫንቃዎችን በኀይል ምቱ። ባደካማችኋቸውም ጊዜ (አትግደሏቸው ማርኳቸው)። ማሰሪያውንም አጥብቁ። በኋላም ወይም በነጻ ትለቋቸዋላችሁ፤ ወይም ትበዧቸዋላችሁ። (ይህም) ጦሪቱ መሳሪያዋን እስከምትጥል ድረስ ነው። (ነገሩ) ይህ ነው። አላህም ቢሻ ከእነርሱ (ያለጦር) በተበቀለ ነበር። ግን ከፊላችሁን በከፊሉ ሊሞክር (በዚህ አዘዛችሁ)። እነዚያንም በአላህ መንገድ ላይ የተገደሉትን ሥራዎቻቸውን ፈጽሞ አያጠፋባቸውም።"(ሙሀመድ 47:4) በማለት በጦርነት ወቅት ሙስሊሞች ምርከኞች ጦርነቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ አጥቀው እንዲይዙ ያዛል። ጦርነቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ሙስሊሞች ያለውን ነባራዊ ሁኔታ፣ ጥቅምና ጉዳትን ካመዛዘኑ በኋላ ምርኮኞችን አስመልክቶ አራት ምርጫዎች ተሰጥቷቸዋል።

1, በነፃ መልቀቅ

2, ምርኮኛን በምርኮኛ መለዋወጥ፣ ካሳ (ቤዛ) ከፍሎ ነፃ የሚወጣም ካለ ነፃ እንዲወጣ ማድረግ

3, በልዩ ሁኔታ መገደል ያለባቸው ካሉ መግደል ለምሳሌ፦ ቀድሞ በነፃ ተለቆ በድጋሜ የተማረከ

4, ባሪያ አድርጎ መያዝ

ጥያቄ የሚነሳው በአራተኛው ምርጫ ነው። ሙስሊሞች ነባራዊ ሁኔታውን እንዲሁም ጥቅምና ጉዳትን አመዛዝነው ከምርከኞች በነፃ የሚለቁትን ለቀው፤ በቤዛ የወሰደውን ሰደው፤ በልዩ ምክንያት መገደል ያለበትን ወይም ከሀገር መሰደድ ያለበትን ከወሰኑ በኋላ የቀሩትን ባሪያ ያደርጋሉ። ምክንያቱም

ሀ, ለጦርነት ሊገድሉ ወይም ሊማርኩ የመጡ ጠላቶችን ማርኮ ነፃ መልቀቅ መልሶ እንዲወጋ ማበረታታት ነው። በለስ ባይቀናው እንጂ የመጣበት ዓላማ እስልምናን ሊያጠፋ፣ ነቢዩንና ባልደረቦቻቸውን ሊገድል፣ ባሪያ ሊፈነግል ነው። ስለዚህ

*ኢብኑ ዐብ-ባስ ይህን አንቀፅ አስመልክቶ እንዲህ ይላሉ፦ "የዛኔ ምርኮኞቻቸው አጋሪያን ነበሩ።"*[47] *ኢብኑ ከሢር አያይዘው እንዲህ ይላሉ፦ "ለዚህ (ትርጓሜ) የሚመሰክረው መልዕክተኛው በበድር ዘመቻ ወቅት ምርኮኞችን እንዲንከባከቡ ሰሓቦቻችውን ማዘዛቸው ነው፤ እነርሱም በምግብ ወቅት ከራሳቸው ያስቀድሟቸው ነበር!"አቡ ዑዘይር ኢብኑ ዑመይር ኢስላምን ሳይቀበልበፊት ስላጋጠመው ተያያዥ ጉዳይ እንዲህ ሲል ይመሰክራል፦"በበድር ጦርነት ከተማረኩት መካከል ነበርኩ፤ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ አሉ፦ "ለምርኮኞች መልካም የመዋልን አደራ ጠብቁ!" እኔም ከአንሷር ጭፍራዎች ጋር ነበርኩ፤ ቁርሳቸውንና እራታቸውን ባቀረቡ ጊዜ በመልዕክተኛው አደራ የተነሳ እነርሱ ቴምር በልተው እኔን ዳቦ ያበሉኝ ነበር!"*[48] *ታዲያ ይህ ሁሉ ገደብና ፍትህ በጦርነት ዘመቻ ላይ ከሆነ ጭራሽ*

---

ሊገድል የመጣን ምርኮኛ ነፃ አድርጎ መላክ አንገት ላይ ገመድ እንደመጠምጠም ይሆናል። በእድሜው የገፋ ወይም በሙስሊሞች ግምገማ በነፃ የሚለቀቁ እንዳሉ ሁሉ።

ለ, በነቢዩ ﷺ ዘመን አጥፊዎች የሚቀጡበት ማረሚያ ቤት አልነበረም። ነቢዩ አጥፊዎች ሲመጡ የሙስሊሞችን አምልኮና ሥነ-ምግባር ይማሩ ዘንድ መስጂድ ነበር የሚያስቀምጧቸው። የጦር ምርከኞችን ሁሉ መስጅድ ሰብስበው ቢያስገቡ እነርሱን መመገብ የሚያስችል አቅም አልነበራቸውም። ስለዚህ ምርከኞችን በየሙስሊሙ ቤት በትኖ እየሰሩ እንዲበሉ ማድረግ ግድ ነው። እስልምናን ሊያጠፉ መጥተው ምርኮ የሆኑ በርካታ ባሮች የሙስሊሞችን አምልኮና ሥነ-ምግባር ሲያዩ እስልምናን እንዲወዱ አድርጓቸው ሰልመዋል።

ሐ, አንድ የቀረ ምርጫ ግን አለ። በለስ ባይቀናው እንጂ እስልምናን ሊያጠፋ፣ ነቢዩንና ሙስሊሞችን ሊገድ የመጣን ሰው ነፃ መልቀቅ የማይቻል ከሆነና ባሪያ ሆኖ አሳዳሪው ከሚበላው በልቶ፣ እንደ አሳዳሪው ለብሶ መኖር ኢ-አመክኗይ አይደለም ካልን ሶስተኛው ምርጫ ምርኮኛ ነውና አሰቃይቶ መረጃ አስወጥቶ መግደል ተገቢና አመክኗዊ ተግባር ነው። (የዘመናችንን የምርኮኛ አያያዝ ከነብዩ አስተምህሮት ጋር አነፃፅሩት) ሊገድል መጣ፣ ካልገደለ መገደሉ እጣ ፈንታው ነው።"ከመሞት መሰንበት"ነውና ኢስላም ባርነታቸውን መርጧል። በኢስላም ባሮች ከባርነታቸው የሚወጡባቸውን በርካታ መንገዶች ትንቢተ ነቢዩ ሙሀመድ በሚለው መፅሀፌ 218-230 በሰፊው ስለፃፍኩት ይመልከቱ!

[46] አል-ኢንሳን 76፡ 8

[47] ተፍሲር ኢብኒ ከሢር (8/288)

[48] አጥ-ጦበራኒ በሁለቱ ሙዕጀሞች ዘግበውታል፦ "መጅመዑ'ዝ-ዘዋኢድ" ቁጥር 10007 ይመልከቱ፤ በተጨማሪም "ሲረቱ ኢብኒ ሂሻም" (1/645) ይመልከቱ።

*በሰላሙ አለም ደግሞ ወሰን የመተላለፍ ክልከላው እጅግ የበረታና የፀና መሆኑ አያጠራጥርም።*

*አዎን! ይህ ነው የኛ ኢስላም!"*

## ጂሐድ በ"ፍትሐዊያን" ዓይን

አንድ ክርስቲያን ፀሀፊ እንዲህ ሲል አስፍሯል *"ሙሃመድ ወደ ሃይል እርምጃና ወደ ጦርነት የሚገባው ሌላ የተሻለ አማራጭ በፍፁም ደረጃ በሚያጣበት ጊዜና ያውም በማመንታት አግባብ ጦርነትን እየጠላው ብቻ ነው። ሙሃመድ ጦርነት ማካሄድን የሚመርጠው በሁሉም የልበ-ብርሃን በሳልና ሠላማዊ አማራጭ መንገዶች በኩል በሚገባ ከሄደ በኋላ ብቻ ነበር። እርሱ አንድም ጊዜም ቢሆን በሠይፉ አስቦ አያውቅም፤ ሠይፉንም ስሎ አያውቅም - የመጨረሻው ዝግ አማራጭ ቢገጥመው እንጅ። ጦርነት ውስጥ የሚገባውም በራስ መከላከል እርምጃነት ብቻ ነበርም። ሙሃመድ በጦር ሜዳ ላይ ተገኝቶም ጭምር ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ለጠላቶቹ የሠላም አማራጭ ከማቅረብ ወደ ኋላ ብሎ አያውቅም ነበር። የጠላት ጦር ማንኛውም መብቶች ላይ ወረራ ፈጽሞም ከቶ አያውቅም። የእርሱ የምንጊዜም ጥያቄ የነበረውም ከእነርሱ ምንም ነገር እንደማይፈልግ ብቻ ሆኖ ነገር ግን የነቢይነቱን ሚና ይጫወት ዘንድ እንዲፈቅዱለት ብቻ ነበር። ይህንን ፈቃደኝነት እንዲላበሱም ያበረታታቸው እና ያተጋቸውም ነበር። ለዚህ ስኬታማነት ሲልም ምኀረት ያደርጋል፤ ለጥያቄአቸው ፈቃደኛ ይሆናል፤ እንዲሁም በእነርሱ ላይ እምነት እንዳለው ያሳያል። ነገር ግን ሙሃመድ በዘልማዱ የጣኦት አምልኮ ቀጣይነት ፍላጎትን ይቃወማል። ይህንን አቋም የሚያራምድበት ምክንያትም የእርሱ*

*ሚና ጋር አብሮ የማይሄድና ከፈጣሪ በብቸኝነት መመለክ የተገባው የመሆኑ መልዕክቱ ጋር የሚቃረን በመሆኑ ነው።*

*በጥቅሉ ሲስተዋል በሙሃመድ የአካሄድ አግባብና አመራር ላይ ምንም ዓይነት ክፍተት እና ግጭት አናይም። ለሃይማኖቱ ግቡን መምታት ሲባል እንደተፈፀመ የተመዘገበ ምንም ዓይነት ጅምላ ጭፍጨፋ እና ጅምላ ግድያ ፈጽሞ አልነበረም። በአንፃራዊ አተያይም አምባገነን ስነምግባር አልነበረውም።*"[49]

እኤአ 1795 እስከ 1881 የኖረው እንግሊዛዊው ፀሀፊ ቶማስ ካርሊልም በበኩሉ"ሙሐመድ ጥሪውን በጎራዴ ተጠቅሞ እንዲቀበሉ አድርጎዋል የሚለው አባባል ትክክለኛ አባባል አይደለም። ማንም ሰው ጎራዴውን በማንሳት በመጋደል ጥሪውን እንዲቀበሉ ማድረግ አይችልም። መቀበል የቻሉት አምነውበት ብቻ ነበር። ጥሪውን ያለተቀበሉ ጠላቶች ከሚያሸንፋቸው በፊት ጥሪውን ተቀብለዋል። ብዙ ሰዎች ሙሐመድ ጥሪውን ማስተላለፍ በጀመረበት ጊዜ ጎራዴን ተጠቅሞዋል የሚል አባባል አላቸው ይህ ትልቅ ስህተት ነበር።"[50] በማለት "ሙሀመድ በሰይፍ ኃይል አስልመዋል" የሚለውን ክስ ውድቅ አድርጎታል።

እውቁ የህንድ የነፃነት ታጋይ ማሀተመ ጋንዲምም"እርግጠኛ ሁኘ የተቀበልኩት ነገር ቢኖር እስልምና ከብሩን ያገኘው በጎራዴ አለመሆኑን ነው። ግን ይህን ክብር ያገኘው የሙሐመድ ፈገግታ እና ገራገር መሆን እንዲሁም ታማኝነት በተጨማሪም ለተከታዮቹ እና ለወዳጆቹ ግልጽ እና ታማኝ መሆን እንዲሁም በፈጣሪው እና ይዞ በመጣው መልእክት ያለው ጥብቅ እምነት እና ጀግና መሆኑ ነው። ይህ ባህሪው ነው መንገዱን ያመቻቸለት እንቅፋቶችንም ያገለለለት ሰይፍ ሳይሆን ይህ ጥሩ

[49] የሙሐመዳዊነት የእምነት ነፀብራቅና የሙሐመድ አመራር፡ ደራሲው ያልታወቀ፡ ገፅ 16

[50] እስልምና እና ዓለማችን፡ አደም ካሚል፡ ገፅ 132

ባህሪው ነው"ሲል የነቢዩ መሐመድ የስኬት ምንጭ ጎራዴ ሳይሆን መልካም ስነ-ምግባር መሆኑን ገልጿል፡፡[51]

## ኊልቆ ሰማዕታት

እስልምናና ነቢዩ ሙህመድ አስገድዶ ከማስለም[52] ፍፁም የራቁ ሲሆን ነቢዩ ያደረጓቸው ሁሉም ጦርነቶች ራስን ለመከላከል የተደረጉና ግዛትን ለማስመለስና

[51] ዝኒ ከማሁ፡ ገፅ 147-148

[52] ከአስገድዶ ማስለም ጋር ተያይዞ የሚነሳው"ከእስልምና የወጡ ወገኖች ለምን ይገደላሉ? መገደላቸውስ በሀይማኖት ማስገደድ አይደል ወይ?"የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ እንደሚታዎቀው እስልምና በነቢዩ ሙሀመድ ዳግም ሲሰበክና ተከታዮችን ሲያፈራ መንግስታዊ ሀይማኖት ሆኗል፡፡ አካባቢያዊ አሰላለፉም የኢ አማኒያን መንግስት በአንድ ጎን የሙስሊሞች መንግስት ደግሞ በሌላ ጎን እንዲሆን አስችሎታል፡፡ ይህ እንግዲህ በእያንዳንዱ አማኝና ኢ-አማኝ ያለውን ትፅዕኖ የተለየ እንዲሆን አስችሏል፡፡ ስለሆነም የአንድ ሰው ከእስልምና መውጣት በአላህ ዘንድ ትልቅ ወንጀል ከመሆኑም ባሻገር ለዘመኑ የመንግስት አሰላለፍ ትልቅ አንድምታ አለው፡፡ አንድ ሰው ከእስልምና ወጥቷል ማለት የፖለቲካ ክህደት ፈፅሟል (political treason)፣ ህዝብን አሳምጿል (public rebellion)፣ ሚስጥር ለጠላት አሳልፏል (Leaking state secrets to the enemy)፣ ኢስላማዊ መንግስትን አዳክሟል (ክዷል) (Undermining the Muslim state)፣ ከጠላት ኃይል ጋር አብሯል (Joining hostile forces) ማለት ነው፡፡ ነቢዩ ሙሀመድ"የሙስሊም ደም ከሶስት ነገሮች ውጭ አይፈስም (አይገደልም) ያገባ ዝሙተኛ፣ ነፍስ ያጠፋ፣ ከእስልምና ወጥቶ ጀመዓ (ስብስብ) የበተነ (ቢሆኑ እንጂ)"(ሙስሊም 1676፣ ቡኻሪ 6878) በማለታቸው ከእስልምና የወጣ ለምን እንደሚገደል እውነታን ያስገነዝበናል፡፡ ስለዚህ ከእስልምና መውጣቱ ሳይሆን የሚያስገድለው መንግስትን መክዳቱ፣ ከጠላት ማበሩ፣ ህዝብን ማሳመፁና የመንግስትን ሚስጥር ለጠላት ማሳለፉ ነው፡፡ ለዚህ ነቢዩ ሙሀመድ ጥቅል በሆነ አነጋገር"ሀይማኖቱን የቀየረን ግደሉት"(ቡኻሪ 6922) ብለዋል፡፡ ሙስሊም ፀሀፊያን የመሰል ሀዲሶች መልዕክት የተፈለገበት የእምነት መለወጡ ሳይሆን ከእምነት መለወጡ ባሻገር ያለው የፖለቲካ አሰላለፍ ጉዳይ መሆኑን ለማስረዳት ከሚጠቅሷቸው መረጃዎች አንዱ የሚከተለው ሀዲስ ነው፡፡"አንድ የገጠር ሰው (በደዊ) ከነቢዩ ጋር ቃል ኪዳን (በይዓህ) ይገባል፡፡ ሆኖም ትኩሳት (ህመም) ያዘውና ከቃል ኪዳኔ ነፃ አድርጉኝ ሲል ጠየቀ፡፡ ነቢዩ እምቢ አሉት፡፡ ደግሞ ጠቀየ እምቢ አሉት፡፡ ተነስቶም ሄደ (ከመድና ውጣ)፡፡ ነቢዩም መድናኮ እንደ ወናፍ ናት ቆሻሻዎችን ታስወግዳለች አሉ፡፡"(ቡኻሪ፡ 1883) በዚህ ሀዲስ እንደተጠቀሰው መድና የፖለቲካና የሀይማኖት ማዕከል በመሆኗ በደዊው ወደ እስልምና የመግባት ብቻ ሳይሆን የገባው ስምምነት ፖለቲካዊም ጭምር ነው፡፡ ሆኖም የመድና አየር ለእንግዳ አትመችምና ስለታመመ ከእስልምና ለመውጣትና ለመመለስ ጠይቋል፡፡ ጉዳዩ የእምነት ጉዳይ ነውና ነቢዩ እምቢ ብለውታል፡፡ ተነስቶ ሲሄድ ግን ምንን ዓይነት ፖለቲካዊ ለውጥ የማምጣት አቅም አለመኖሩን ተረድተው እንዲታሰር ወይም እንዲገደል አላዘዙም፡፡ ይህም ነቢዩ"ሀይማኖቱን የቀየር ግደሉ"ሲሉ ያዘዙት ፖለቲካዊ አሰላለፉ ላይ ሚና ያለውን መሆኑን እንጂ ከእምነት በመውጣቱ አለመሆኑን በግልፅ ያሳያል፡፡

ከእስልምናው ወጣ ስንል እምነትን መቀየር በመፅሀፍ ቅዱስ የሚያስገድል ትልቅ ወንጀል መሆኑን መፅሀፍ ቅዱስ ይነግረናል፡፡ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል"የእናትህ ልጅ ወንድምህ ወይም ወንድ ልጅህ ወይም ሴት ልጅህ ወይም

ለመቆጣጠር[53] የተደረጉ ብቻ ነበሩ። ሆኖም ከከሀዲያን በኩል የተደረገው ጥቃት ሀይማኖትን መሰረት ያደረገ ነውና ነቢዩም ራሳቸውን የተከላከሉት መሰረታቸውን

በብብትህ ያለች ሚስትህ ወይም እንደ ነፍስህ ያለ ወዳጅህ በስውር። ና፥ ሄደን ከምድር ዳር ጀምሮ እስከ ምድር ዳር ድረስ ወደ አንተ የቀረቡት ከአንተም የራቁት አንተን ከብበውህ ያሉ አሕዛብ ከሚያመልኩአቸው አማልክት፥ አንተም አባቶችህም የማታውቋቸውን ሌሎች አማልክት እናምልክ ብሎ ቢያስትህ፥ እሺ አትበለው፥ አትስማውም፤ ዓይንህም አይራራለት፥ አትማረውም፥ አትሸሽገውም፤ ነገር ግን ፈጽመህ ግደለው፤ እርሱን ለመግደል በፊት የአንተ እጅ፥ ከዚያም በኋላ የሕዝቡ ሁሉ እጅ በላዩ ትሁን። ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ካወጣህ ከአምላክህ ከእግዚአብሔር ሊያርቅህ ወድዶአልና እስኪሞት ድረስ በድንጋይ ውገረው።"(ኦሪት ዘዳግም 13፡ 6-10) ዝቅ ብሎም"አምላክህ እግዚአብሔር ልትኖርባት በሚሰጥህ በአንዲቱ ከተማህ። ክፉተኞች ሰዎች ከእናንተ ዘንድ ወጥተው። ሄደን የማታውቋቸውን ሌሎችን አማልክት እናምልክ ብለው የከተማቸውን ሰዎች አሳቱ ሲሉ ወሬ ብትሰማ፥ ትፈልጋለህ፥ ትመረምራለህም፥ ትጠይቃለህም፤ እነሆም፥ እውነት ቢሆን፥ ይህም ክፉ ነገር በመካከልህ እንደ ተደረገ እርግጥ ሆኖ ቢገኝ፥ የዚያችን ከተማ ሰዎች በሰይፍ ስለት ፈጽሞ ትመታቸዋለህ፤ ከተማይቱን፥ በእርስዋም ያለውን ሁሉ፥ እንስሳውንም በሰይፍ ስለት ታጠፋቸዋለህ።"(ኦሪት ዘዳግም ምዕ. 13፡ 13-15) ይላል። በሌላ አንቀፅም"አምላክህ እግዚአብሔር ከሰጠህ ከአገርህ ደጆች በማንኛይቱም ውስጥ ወንድ ወይም ሴት ቢሆን ቃል ኪዳኑን በማፍረስ በአምላክህ በእግዚአብሔር ፊት ክፉት የሠራ ቢገኝ ሄዶም ሌሎች አማልክትን ያመለከ፥ እኔ ላላዘዝኋቸው ለፀሐይና ለጨረቃ ለሰማይም ሠራዊት ሁሉ የሰገደ ቢገኝ፥ ቢያወሩልህም ብትሰማም፥ ያንን ፈጽመህ መርምር፤ እነሆም፥ እውነት ቢሆን፥ በእስራኤልም መካከል እንዲህ ያለ ርኵሰት እንደ ተሠራ እርግጥ ሆኖ ቢገኝ፥ ይህን ክፉ ነገር የሠሩትን ያን ወንድ ወይም ያችን ሴት ወደ በርህ ታመጣቸዋለህ፥ እስኪሞቱም ድረስ በድንጋይ ትወግራቸዋለህ።" (ኦሪት ዘዳግም 17፡ 2-5) በሌላ ቦታም"የአገር ልጅ ቢሆን ወይም መጻተኛ ቢሆን፥ አንዳች በትዕቢት የሚያደርግ ሰው እግዚአብሔርን ሰድቦአል፤ ያም ሰው ከሕዝቡ መካከል ተለይቶ ይጠፋል። የእግዚአብሔርን ቃል ስለ ናቀ፥ ትእዛዙንም ስለ ሰበረ፥ ያ ሰው ፈጽሞ ይጥፋ፤ ኃጢአቱ በራሱ ላይ ነው።" (ኦሪት ዘኍልቍ 15:30-31) ይላል። ለእነዚህና መሰል በርካታ አንቀፆች ማብራሪያ መስጠት ሳያስፈልግ ከእምነት የወጣ ሁሉ እንዲገደል መፅሀፍ ቅዱስ ያዛል። አንዳንድ የዋሆች "አንቀፆቹ ተሽረዋል" ሊሉ ስለሚችሉ አንድ መሰረታዊ ፅንሰ ሀሳብ ላምጣ። ከላይ እንደጠቀስነው ክርስቲያን ሊቃውንት የብሉይ ኪዳን ህጎችን የማህበራዊ (civil/social)፣ የክብረ በዓላዊ (ceremonial/religious) እንድሁም የግብረ-ገባዊ (moral/ethical) በማለት በሶስት ይከፍሏቸዋል። በመፅሀፍ ቅዱስ እምነት የቀየሩ ወገኖች እንዲገደሉ የተደረገው ለፖለቲካ አሰላለፍ ነው እንበል (ካልሆነማ በክርስትና የእምነት ነፃነት የለም ልንል ነው)። አስተዳደራዊ (civil laws) ህጎች ደግሞ ክርስቲያን ነገስታት የሚያስተዳድሩባቸው ህጎች በመሆናቸው ክርስቲያናዊ መንግስት እስኪመሰረት ላይጠቀሙባቸው ይችላል እንጂ ፈፅሞ ሊሻሩ አይችሉም (አራት ነጥብ)።

[53] ታዋቂው የታሪክ ፀሀፊ አቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ግዛት ማስፋፋትን አስመልክቶ ሲፅፉ"*ከባርነት ከወጡ በኋላ ሌላውን ባሪያ ለማድረግ መነሳት በግብፃዊያን አልተጀመረም። በባቢሎንም፣ አሶርም፣ ፋርስም፣ ግሪክም፣ ሮማም፣ ዓረብም የዛሬም ፈረንጆች በሌላው ሲገዙ ኖረው ሌላውን መልሶ ለመግዛት በመመኘት በዚህ ረገድ ያላቸው የታሪክ መስመር የሁሉም አንድ ዓይነት ነው። ካልደከመና ካልፈራ በቀር ሲቻለው የራሴ አገር ይበቃኛል ብሎ በራሱ አገር ተሰብስቦ የኖረ ህዝብና መሪ በታሪክ ውስጥ አይገኝም። በሰው መገዛት መሮኛልና እኔም የሰው አገር አልወርም የሚል ለመውረር አቅሙን ያልተማመነው ብቻ ነው።*" (የኢትዮጵያ ታሪክ ፡ኑቢያ - አክሱም፡ ገፅ 62-63) በማለት ጠንካራ የሆነ አስተዳደር ግዛቱን ማስፋትና ሌሎችን ማስገበር በሁሉም ስልጣኔዎች ዘንድ የተለመደ ተግባር እንደነበር ፅፈዋል። ሙስሊሞችም በተመሳሳይ የስልጣኔ ጫፍ ላይ ሲደርሱ ሀይማኖታቸውን ለመስበክ ችግር እንዳይገጥማቸው መስመር ሊጠርጉ፣ የማዕድን ሀብታቸውን ለመጨመር፣ የንግድ መስመር ለመዘርጋት፣ የተከታዮቻቸውን ቁጥር ለማብዛት የግዛት ማስፋፋት ጦርነቶችን አድርገዋል። የሙስሊሞች የግዛት

ሀይማኖታቸው ላይ አድርገው ነበር። ብዙዎች የነቢዩን የመከላከል የጦር ሜዳ ውሎዎች በሙሉ አስገድዶ ለማስለምና ሆን ብለው ከሀዲያንን ለመጨፍጨፍ የታለሙ እንደሆኑ ስለሚያስቡና "ጭፍጨፋ" የሚሉትንም አጋነው ስለሚያቀርቡ እውነታው ሁሉ የውሸት ጥላሸት ለብሶ እንዳይቀር በማስረጃ ሳሙና ለማጠብና ለማፅዳት ያክል በታሪክ መዛግብት የተገኙ አጠቃላይ የሟቾችን ቁጥር ማቅረብ አስፈላጊ ነው። የነቢዩን ታሪክ ያቀረቡ ፀሀፊያን ነቢዩ ስላደረጓቸው ጦርነቶች ሲዘግቡ አጠቃላይ የሟቾችን ቁጥር ስላሰፈሩ በእያንዳንዱ ጦርነት የተሰው የሟቾችን ቁጥር እንደሚከተለው አስፍሬያለሁ።

| የጦርነቱ ስም | የሙስሊም ሰማእታት ቁጥር | የሌሎች ሙታን ቁጥር |
|---|---|---|
| በድር | 14 | 70 |
| ኡሁድ | 70 | 23 |
| አህዛብ | 6 | 3 |
| በኒ ሙስጦሊቅ | 0 | 3 |
| ኸይበር | 19 | 0 |
| ቢእር መዑናህ | 69 | 0 |
| ሙእታህ | 14 | 14 |
| ሁነይን | 4 | 71 |

ማስፋፋት ከሌሎቹ የሚለው አንድንም ማህበረሰብ በግድ አለማስለማቸው ነው። ልዩነቱን ለማወቅ የቤዛንታይን ኢምፓየርን የግዛት ማስፋፋትና አስገድዶ ጠመቃ ማየት ይቻላል።

| | | |
|---|---|---|
| ጧኢፍ | 13 | 0 |
| ሌሎች | 118 | 256 |
| ድምር | 317 | 439 |

አጠቃላይ የሟቹ ቁጥር = 756 [54]

ይህን ያክል ሰው የሞተበትን "ጦርነት" ነው አጋነው ለጥጠውና አስፍተው "የጭካኔ ጥግ" ላይ ለማድረስ የታተሩት። በዓለም ላይ ጦርነት ተብሎ ብዙ ዓመት ተዋግተው ዝቅተኛ (ምንም ሊባል የሚችል) ሰብዓዊ ኪሳራ ያደረሰ ጦርነት ነቢዩ ሙሀመድ ያደረጓቸው ጦርነቶች ናቸው ማለት ይቻላል። እውነታውን በንፅፅር ለማስረፅ ያክል አለፍ ብየ በሙሴና እያሱ ዘመን እስራኤላዊያን ከግብፅ እስከ ከነዓን ባደረጉት ጉዞ የተገደሉ፣ የወደሙ ንብረቶችንና ሰብዓዊ ኪሳራውን ለመጠቆም እሞክራለሁ።

ራሳቸው በመረጡት ዳኛ በተፈረደ ፍርድ የተገደሉትን የበኒ ቁረይዟ[55] ጎሳ አባላትን አላካተትኩም። ምክንያቱም በኒ ቁረይዟዎች የተገደሉት በፍርድ እንጂ በጦር ሜዳ ስላልሆነ ከጦር ተገዳዮች አይቆጠሩም።

54 ረሒቀል መኽቱም፡ መግቢያ

55 በኑ ቁረይዟህ መድና አካባቢ ካሉና ከሙስሊሞች ጋር ቃል ኪዳን ገብተው ከሚኖሩ የአይሁድ ጎሳዎች አንዱ ናቸው። ሆኖም በአህዛብ ጦርነት ቃልኪዳናቸውን በመጣስ ከነቢዩ ጠላቶች ጋር በመተባበር ሙስሊሞችን ከምድረ ገፅ ለማጥፋት ዶልተዋል። ከድል በኋላም ቃል ኪዳናቸውን በመጣሳቸው ሰእድ ኢብኑ ሙአዝን ዳኛ አድርገው በመምረጥ በመረጡት ዳኛ ፍርድ አማካኝነት የተገደሉ ናቸው። ምንም ከሳሾች የበኑ ቁረይዟን ግድያ አንዳንድ ጊዜ አስገድዶ ከማስለም፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ከዘረኝነት ጋር አያይዘው አይሁድ ስለሆኑ ነው ቢሉም እውነታው ግን የተገደሉት እራሳቸው በመረጡት ዳኛ ፍርድ የገቡትን ቃል ኪዳን ስላፈረሱና ሙስሊሞችን ከምድረ ገፅ ለማጥፋት ስለተባበሩ ነው። ኢብኑ ቁረይዟዎች ለአህዛብ ጦርነት አንድ ሺህ አምስት መቶ ሰይፍ፣ ሁለት ሺህ ጦር፣ ሦስት መቶ ጡሩር፤ አምስት መቶ ጋሻና ጦር አከማችተው ነበር። (ሙሉ ታሪኩን ትንቢተ ነቢዩ ሙሀመድ፡ ንፅፅራዊ አቀራረብ፡ ገፅ 254-256 ይመልከቱ)

# የእስራኤላዊያን ጉዞና የፍስጤማዊያን መጨፍጨፍ

እስራኤላዊያንን ከግብፅ እንዲወጡ ያዘዘው እግዚአብሔር በከነዓንና በአካባቢው ያሉ ህዝቦችን አስለቅቆ ሳይሆን በጦር ኃይል አስጨፍጭፎ እንደሚሰጣቸው ለእስራኤላዊያን በተደጋጋሚ ቃል ገብቶ ነበር። መፅሀፉ በብዙ ቦታዎች ይህንኑ እውነት ቁልጭ አድርጎ ነግሮናል።"እኔም ከአንተ አስቀድሜ መልአክ በመላክ ከነአናውያንን፣ አሞራውያንን፣ ሂታውያንን፣ ፈሪዛውያንን፣ ሂዋውያንንና ኢያቡሳውያንን አስወጣለሁ።"[56] በሌላ አንቀፅም "አምላክህ ይሖዋ ርስት አድርገህ ወደምትወርሳት ምድር ሲያመጣህ ብዙ ሕዝብ ያላቸውን ብሔራት ይኸውም ከአንተ ይልቅ ብዙ ሕዝብ ያላቸውንና ኃያላን የሆኑትን ሰባት ብሔራት ማለትም ሂታውያንን፣ ገርጌሻውያንን፣ አሞራውያንን፣ ከነአናውያንን፣ ፈሪዛውያንን፣ ሂዋውያንን እና ኢያቡሳውያንን ከፊትህ ያስወግድልሃል።"[57] እንድሁም "አምላክህ ይሖዋ ርስት አድርገህ ወደምትወርሳት ምድር ሲያመጣህ ብዙ ሕዝብ ያላቸውን ብሔራት ይኸውም ከአንተ ይልቅ ብዙ ሕዝብ ያላቸውንና ኃያላን የሆኑትን ሰባት ብሔራት ማለትም ሂታውያንን፣ ገርጌሻውያንን፣ አሞራውያንን፣ ከነአናውያንን፣ ፈሪዛውያንን፣ ሂዋውያንን እና ኢያቡሳውያንን ከፊትህ ያስወግድልሃል።"[58] እያሱም በተመሳሳይ "እሱም ከነአናውያንን፣ ሂታውያንን፣ ሂዋውያንን፣ ፈሪዛውያንን፣ ገርጌሻውያንን፣ አሞራውያንንና ኢያቡሳውያንን በእርግጥ ከፊታችሁ እንደሚያባርራቸው በዚህ

[56] ዘፀአት 33:2

[57] ዘዳግም 7:1

[58] ዘዳግም 7:1

ታውቃላችሁ።"[59] በማለት ነባር ነዋሪዎችን በማስለቀቅ ሀገር እንደሚሰጣቸው ይናገራል። እነዚህ ነባር ነዋሪዎች ከእስራኤላዊያን ጋር የማይተዋወቁ ሰላማዊ ነዋሪዎች ነበሩ። መፅሀፉም "ሙሴንም እንዲህ አሉት፦ "ወደላክኸን ምድር ገብተን ነበር፤ በእርግጥም ምድሪቱ ወተትና ማር የምታፈስ ናት፤ የምድሪቱም ፍሬ ይህን ይመስላል። ይሁንና በምድሪቱ የሚኖሩት ሰዎች ብርቱዎች ናቸው፤ በግንብ የታጠሩት ከተሞችም ቢሆኑ በጣም ታላላቅ ናቸው። ደግሞም ኤናቃውያንን በዚያ አይተናል። አማሌቃውያን በኔጌብ ምድር ይኖራሉ፤ ሂታውያን፣ ኢያቡሳውያንና አሞራውያን ደግሞ በተራራማው አካባቢ ይኖራሉ፤ በባሕሩ አካባቢና በዮርዳኖስ ዳርቻ ደግሞ ከነአናውያን ይኖራሉ።"[60] እንዳለው የተስፋይቱ አገር ነባር ነዋሪዎች ብርቱዎችና ታላላቅ ከተሞችን መገንባት የቻሉ የሰለጠኑ ህዝቦች ነበሩ።

ሆኖም እግዚአብሔር የነዚህን ህዝቦች መኖር አልወደደም"እስራኤላውያንን ተናገራቸው፤ እንዲህም በላቸው፦ 'እንግዲህ ዮርዳኖስን ተሻግራችሁ ወደ ከነአን ምድር ልትገቡ ነው። የምድሪቱን ነዋሪዎች በሙሉ ከፊታችሁ አባሯቸው፤"[61] በሌላ አንቀፅም "ከዚያም ዮርዳኖስን ተሻግራችሁ ወደ ኢያሪኮ መጣችሁ። የኢያሪኮ መሪዎች የሆኑት አሞራውያን፣ ፈሪዛውያን፣ ከነአናውያን፣ ሂታውያን፣ ገርጌሻውያን፣ ሂዋውያንና ኢያቡሳውያን ተዋጓችሁ፤ እኔ ግን እነሱን በእጃችሁ አሳልፌ ሰጠኋችሁ።"[62] በተመሳሳይም "አምላክህ ይሖዋ ርስት አድርጎ በሚሰጥህ እነዚህ ሕዝቦች በሚኖሩባቸው ከተሞች ውስጥ ግን እስትንፋስ ያለውን ማንኛውንም ነገር

[59] እያሱ 3:10

[60] ኦሪት ዘኁልቁ 13:27-30

[61] ዘኁልቁ 33:50-51

[62] እያሱ 21:11

በሕይወት አታስቀር። ከዚህ ይልቅ አምላክህ ይሖዋ ባዘዘህ መሠረት ሂታውያንን፣ አሞራውያንን፣ ከነአናውያንን፣ ፈሪዛውያንን፣ ሂዋውያንንና ኢያቡሳውያንን ሙሉ በሙሉ አጥፋ፤"በማለት ላያችው አልፈልግምና አጥፉልኝ ሲል አዘዘ። ተሳስተው በህይዎት እንዳይተዋቸውና እንዳይዛመዷቸውም"የምድሪቱን ነዋሪዎች ከፊታችሁ ሳታባርሩ እዚያው ከተዋችኋቸው ግን ዓይናችሁ ውስጥ እንደገባ ጉድፍ እንዲሁም ጎናችሁ ላይ እንደተሰካ እሾህ ይሆኑባችኋል፤ ደግሞም በምትኖሩበት ምድር ያንገላቷችኋል።" [63] በማለት ጥላቻውን በግልፅ የሚያሳይና አንድ እንኳን እንዳያስቀሩ በግልፅ ተናገረ።

በዚህ ቃል መሰረት በመጀመሪያ አሞራዊያንን ወጉ [64] በየከተሞች የነበሩትን አሞራዊያን ሁሉ ከከተሞቻቸው አባረሯቸው[65] ከከተሞቻቸው የተባረሩትን አሞራዊያን እስራኤላዊያን በሌላ ዙር ከአድሱ ከተማቸውም አባረዋቸዋል[66]፤ ቀጥለው የባሳንን ህዝብ አንድም ሰው ሳያስቀሩ ጨፈጨፉ፤[67] ቀጥለው በምዲያማዊያን ላይ ጦርነት በመክፈት ሁሉንም ወንዶች ገደሉ፣ ሴቶችና ህፃናትን በባርነት አጋዙ፣ ከወንድ ጋር ያልተገናኙ ሴቶችን በቁባትነት ተካፈሉ፣ ከተሞቻቸውን በሙሉ አቃጠሉ፣ ንብረቶቻቸውን ሁሉ ዘርፈው መሰዱ፤ [68] ቀጥለው እያሪኮን በመውጋት ከረዓብና ከቤተሰቦቿ ውጭ "በከተማዋ ውስጥ የነበረውን በሙሉ ይኸውም ወንዱንና

[63] ዘኁልቊ 32:55

[64] ዘኁልቊ 21:24

[65] ዘኁልቊ 21:32

[66] ዘኁልቊ 32:39

[67] ዘኁልቊ 21:35፣ ዘዳግም 3:3

[68] ዘኁልቊ 31:7-11

ሴቱን፣ ወጣቱንና ሽማግሌውን እንዲሁም በሬውን፣ በጉንና አህያውን በሰይፍ ሙሉ በሙሉ አጠፉ"[69]፣ ቀጥለው ጋይን በመውረር ሙሉ ህዝቡን ገድለው ከተማይቱንም አቃጠሏት[70] ፀሀፊው የጋይዎችን እልቂት ሲዘግብ "እስራኤላውያን የጋይን ነዋሪዎች በሙሉ ሜዳ ላይ ይኸውም ሲያሳድዷቸው በነበረው ምድረ በዳ ላይ ፈጇቸው፤ አንድም ሳይቀር ሁሉም በሰይፍ አለቁ። ከዚያም እስራኤላውያን በሙሉ ወደ ጋይ ተመልሰው ከተማዋን በሰይፍ መቱ። ወንድ ሴት ሳይል በዚያን ቀን የሞቱት የጋይ ሰዎች በጠቅላላ 12,000 ነበሩ።"[71]፣ ይህን የእስራኤላዊያኑን ጭፍጨፋ የሰሙት አምስቱ የአሞራዊያን መንግስታት የሚባሉት የኢየሩሳሌም ንጉሥ፣ የኬብሮን ንጉሥ፣ የያርሙት ንጉሥ፣ የለኪሶ ንጉሥና የኤግሎን ንጉሥ ተሰባስበው ጦር የገጠሙ ቢሆንም እግዚአብሔር የበረዶ ድንጋይ በማውረድ ገደላቸው፤ የተበታተኑትንም ተከታትለው አጠፏቸው[72]፣ አምስቱ ነገሥታት ባለቁ ዕለት መቄዳን በመውረር ጨርሰው አጠፏቸው[73]፣ ቀጥሎ ሊብናንን በመውርውር"ከተማዋንና በውስጧ ያለውን ሰው ሁሉ አንድም ሳያስቀሩ በሰይፍ መቱ።"[74]፣ ቀጥለው ለኪሶን በመውረር"በሊብና ላይ እንዳደረጉትም ሁሉ ከተማዋንና በውስጧ ያለውን ሰው ሁሉ በሰይፍ መቱ።"[75]፣ የጌዜር ንጉስንም"ኢያሱ እሱንና ሕዝቡን አንድም ሳያስቀር

---

[69] እያሱ 6:21

[70] እያሱ 8:19-22

[71] እያሱ 8:24-25

[72] ኢያሱ 10: 5-11

[73] ኢያሱ 10:28

[74] ኢያሱ 10:30

[75] ኢያሱ 10:32

መታቸው።"[76]፣ ቀጥለው ኤግሎንን በመውርውር"ከተማዋን በመቆጣጠር በሰይፍ መቷት። በለኪሶ ላይ እንዳደረጉት ሁሉ በውስጧ ያለውን ሰው ሁሉ በዚያኑ ዕለት ሙሉ በሙሉ አጠፉ።"[77]፣ ቀጥሎ ኬብሮንን"ተቆጣጥረው ከተማዋን፣ ንጉሥዋንና በዙሪያዋ ያሉትን አነስተኛ ከተሞች እንዲሁም በውስጧ ያለውን ሰው ሁሉ አንድም ሳያስቀሩ በሰይፍ መቱ። በኤግሎንም ላይ እንዳደረገው ሁሉ ከተማዋንና በውስጧ ያለውን ሰው ሁሉ ሙሉ በሙሉ አጠፋ።" [78] ፣ ቀጥለው ደርቢን በመውረር"ከተማዋን፣ ንጉሥዋንና በዙሪያዋ ያሉትን አነስተኛ ከተሞች ተቆጣጠረ፤ እነሱንም በሰይፍ መቷቸው፤ በውስጧ ያለውንም ሰው ሁሉ አንድም ሳያስቀሩ ፈጽመው አጠፉ።"[79]፣ ይህንን የእስራኤል ዘግናኝ ጭፍጨፋ የሰሙት ሌሎች መንግስታት ተሰባስበው የገጠሙ ቢሆንም ድል ለእስራኤላዊያን ሆነና"አንድም ሰው በሕይወት ሳያስቀሩ መቷቸው።"[80] ቀጥለው ሀጾርን በመውረር "በውስጧ ያለውን ሰው ሁሉ በሰይፍ በመምታት ፈጽመው አጠፉ። እስትንፋስ ያለው አንድም ነገር አላስቀሩም።"[81] በኢያሱ ብቻ በተመሳሳይ ሁኔታ ምንም ህይዎት ያለው ፍጡር ሳይቀር የተጨፈጨፉ መንግስታት 31 ሲሆኑ መፅሀፉም "የኢያሪኮ ንጉሥ፥ በቤቴል አጠገብ ያለችው የጋይ ንጉሥ፥ የኢየሩሳሌም ንጉሥ፥ የኬብሮን ንጉሥ፥ የየርሙት ንጉሥ፥ የለኪሶ ንጉሥ፥ የኦዶላም ንጉሥ፥ የጌዝር ንጉሥ፥ የዳቤር ንጉሥ፥ የጌድር ንጉሥ፥ የሔርማ ንጉሥ፥ የዓራድ ንጉሥ፥ የልብና ንጉሥ፥ የዓዶላም ንጉሥ፥

[76] ኢያሱ 10:33

[77] ኢያሱ 10:35

[78] ኢያሱ 10:37

[79] ኢያሱ 10:39

[80] ኢያሱ 11:10

[81] ኢያሱ 11:11

የመቄዳ ንጉሥ፥ የቤቴል ንጉሥ፥ የታጱዋ ንጉሥ፥ የኦፌር ንጉሥ፥ የአፌቅ ንጉሥ፥ የለሸሮን ንጉሥ፥ የማዶን ንጉሥ፥ የአሶር ንጉሥ፥ የሺምሮን ሚሮን ንጉሥ፥ የአዚፍ ንጉሥ፥ የታዕናክ ንጉሥ፥ የመጊዶ ንጉሥ፥ የቃዴስ ንጉሥ፥ በቀርሜሎስ የነበረ የዮቅንዓም ንጉሥ፥ በዶር ኮረብታ የነበረ የዶር ንጉሥ፥ የጌልገላ አሕዛብ ንጉሥ፥ የቲርሳ ንጉሥ፥ ነገሥታቱ ሁሉ ሠላሳ አንድ ናቸው።"በማለት ዘርዝሮ አስቀምጧቸዋል።[82]

እነዚህንና መሰል አንቀፆችን በማሰባጠር ከ200,000 ሰው በላይ እንደተገደለ የሚገምቱ ሊቃውንት አሉ። ይህ ሁሉ ህዝብና መንግስት ያለቀው እንግዲህ እስራኤላዊያንን ለማስፈር ነበር። ሀገር አልባዎችን ባለ ሀገር ለማድረግ ምን ያክል ህዝብና መንግስት እንዳለቀ ከላይ ያሉት ጥቅሶች ብቻ በቂ ናቸው። ዳዊት ይህንን እልቂት ሲደመድም የእስራኤልን ህዝብ ከነዓን ለማስፈር እግዚአብሔር"ብዙ ብሔራትን መታ፤ ኃያላን ነገሥታትንም ገደለ፤ የአሞራውያንን ንጉሥ ሲሖንን፣ የባሳንን ንጉሥ ኦግን፣ የከነአንንም መንግሥታት ሁሉ ድል አደረገ። ምድራቸውን ርስት አድርጎ፣ አዎ፣ ርስት አድርጎ ለሕዝቡ ለእስራኤል ሰጠ።"[83] ብሏል።

## የእስራኤላዊያን ወረራ ባህሪያት

የእስራኤላዊያንን ወረራ ለየት የሚያደርጉት የተለያዩ ባህሪያት ነበሩት።

**፩, ጭፍጨፋው መለኮታዊ መሆኑ፡-** ይህ ሁሉ ጭፍጨፋ ለፖለቲካ አላማ የተፈለገ ሰዋዊ ሳይሆኑ በእግዚአብሔር የታዘዘ መለኮታዊ ፍቃድ ያለው ጭፍጨፋ

[82] ኢያሱ 12፡9-24

[83] መዝሙር 135፡ 10-12

ነው። እግዚአብሔር ራሱ ነው ግደሉ፣ ጨፍጭፉ ብሎ ያዘዘው። እግዚአብሔር ራሱ አንዳንደ ተዋጊ ይሆናል፣ ሌላ ጊዜ አዋጊ ይሆናል፣ ሌላ ጊዜ የውጊያ ቦታ ይመርጣል።

**፪, ህይዎት ያለውን ሁሉ የሚቀጥፍ መሆኑ፡-** በእስራኤላዊያን የተወረረ የትኛውም ሀገር ነዋሪ ትልቅ ትንሽ፣ ህፃን ሽማግሌ፣ ሴት ወንድ ሳይባል ሁሉም ይጨፈጨፋል። በህይዎት ያለ ማንኛውም ሰው ከመሰየፍ ውጪ ምንም አይነት አማራጭ አልተተወለትም። መፅሀፉም "አምላክ እግዚአብሔር ባዘዘውም መሠረት እስትንፋስ ያለውን ሁሉፈጽሞ አጠፋ።"በማለት ሳይደብቅ ነግሮናል።" [84] በሌላ ቦታም "እስራኤላውያን ከእነዚህ ከተሞች ያገኙትን ምርኮና የቤት እንስሳ ሁሉ ለራሳቸው ወሰዱ። ሰዎቹን ግን አንድ በአንድ በሰይፍ መተው ሁሉንም አጠፏቸው። እስትንፋስ ያለው አንድም ሰው አላስቀሩም።"[85] ሲል በኩራት ተናግሯል።

**፫, ምርኮኛ አልባነት፡-** የእስራኤል ወረራ እጅግ ጨፍጫፊ ከመሆኑም በላይ ተሸንፎ የሸሸንም በማሳደድ አንድ በአንድ የገደሉበት ፈፅሞ ምርኮኛ የሌለበት ነበር። ከጦር ሸሽቶ ሌላ ቦታ የሰፈረን ተከታትሎ የሚገድል፣ ፈርቶ ዋሻ የገባን ዋሻ ዘግቶ በርሃብ የሚጨርስ፣ የተማረከን የሚሰይፍ እጅግ ዘግናኝ ጦርነት።

**፬, በእንስሳትም ላይ የተቃጣ መሆኑ፡-** አልፎ አልፎ እንስሳትን ለግል የመውሰድ አጋጣሚ ቢኖርም አብዛኛው የእስራኤላዊያን ወረራ እንስሳትንም የሚያጠፋ ነበር።

[84] ኢያሱ 10:40

[85] ኢያሱ 11:14

መፅሀፉም "ኢያሱ ልክ እግዚአብሔር እንደነገረው አደረገባቸው፤ የፈረሶቻቸውን ቋንጃ"[86] መቁረጣቸውን መዝግቧል። በሌላ ቦታም "በሬውን፣ በጉንና አህያውን በሰይፍ ሙሉ በሙሉ አጠፉ።"[87] በማለት እንስሳትን ሁሉ እንዳወደሙ ገልጿል።

**፫, አውዳሚነት፡-** የእስራኤልን ወረራ ለየት የሚያደርገው አንድም ሰው ሳይቀር ጨፍጭፈው ፎረ አለመኖሩን እያወቁ ከተማ ሳያወድሙ አለመተዋቸው ነው። ሰው ሁሉ እንስሳት ሳይቀር በሰይፍ መተው ከተማውን ለምን እንደሚያቃጥሉ ሌላ ጥናት የሚፈልግ ይመስለኛል።

86 ኢያሱ 10:41

87 ኢያሱ 6:21

# ማጠቃለያ

ኢስላም የሰላም ሀይማኖት ነው። ኢስላም የተማሪና አስተማሪ ሀይማኖት በመሆኑ ሰላምን አጥብቆ ይፈልጋል። ነቢዩ ሙሀመድ ﷺ በበርካታ አስተምሮታቸው ከጦርነትና ከረብሻ እንድንርቅ ወደ ሰላም እንዲንቀርብ አስተምረዋል። ነቢዩ በአንድ ሀዲሳቸው"ጠላትን በጦርነት መገናኘትን አትመኙ። አላህን ሰላም ለምኑት።"[88] ብለዋል። በሌላ ሀዲሳቸውም "ከእናንተ መካከል በነፍሱ፣ በቤቱና በቤተሰቡ ስጋት ሳይኖርበት ሰላም የሆነ፤ አካሉ ከህመም ነፃ የሆነና የዕለት ጉርሻውን ያገኘ ዱንያ በተሟላ መልኩ ለርሱ ተሰብስባለች።"[89] በሌላ አቡ ሁረይራ (ረ.ዐ) ባስተላለፉት ሀዲስ ነቢዩ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ “ከጠላት ጋር መገናኘትን አትመኙ። ካገኛችኋቸው ግን ታገሱ።”[90] ብለዋል። የእስልምና መሰረቱ ይሄ ነው። በተመሳሳይ ከራስ ላይ መከላከልም ሰብዓዊ ተግባር ነው። ጂሀድ በነዚህ መካከል ያለ ድንበር ነው። ሰላምን ለማምጣት እና ከጥቃት ለመከላከል የሚደረግ ጥረት ነው። ይህ የሁሉም ሀይማኖቶች አስተምህሮት በመሆኑ መለኮታዊ መፅሀፍቶቹ በውስጣቸው የሰላም እና ራስን የመከላከል አንቀፆች መኖራቸው ግድ ነው። እንደት ሰላም መፍጠርና እንደት ራስን መከላከል እንደምንችል እንማርባቸዋለንና። በእስልምና ትውፊቶች የምናገኘው እውነትም ይሄው ነው። የጦርነት አናቅፅትን በዚህ ሚዛን ማየት እስልምናንና ሙስሊሞችን ከመውቀስ ያድናል። ሀይማኖታዊ መቀራረብንም ይፈጥራል። የዚህ ፅሁፍ አላማም ይህንን መቀራረብ መፍጠር ነው።

[88] ቡኻሪ 2966፣ ሙስሊም 1742

[89] ቲርሚዚ

[90] ቡኻሪና ሙስሊም